# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ | 81ኛ ዓመት ቁጥር 340 ነሐሴ 10 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ


## «የሥራ ዕድል በመፍጠር አርዓያ እንሆናለን»

-ሙፈሪያት ካሚል
የሥራና ክሂሎት ሚኒስትር

**ውብሸት ሰንደቁ**



ፎቶ - ሐዱሽ አብርሃ

አዲስ አበባ፡- ከእጅ ወደ አፍ የሆነ የሥራ ዕድል ሳይሆን ዘላቂና ጥራት ያለው የሥራ ዕድል በመፍጠር አርዓያ እንሆናለን ሲሉ የሥራና ክሂሎት ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል ገለፁ።በ2014 በጀት ዓመት ለ2 ነጥብ 7 ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን ጠቁመዋል፡፡

ሁለተኛው ብሔራዊ የሥራ ጉባዔ «ዘላቂ ሥራ ለብሩህ ነገ» በሚል መሪ ሃሳብ በትናንትናው ዕለት በተጀመረበት ወቅት የሥራና ክሂሎት ሚኒስትሯ ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል ባደረጉት ንግግር፤ በአሁኑ ጊዜ ሥራና ሠራተኛ በወጉ እየተገናኙ አይደለም፤ ይህን ችግር ለመፍታት በቴክኒክና ሙያ ተቋማት ሥርዓተ ሥልጠናዎች የገበያውን ፍላጎት መሠረት ያደረጉ እንዲሆኑ ይደረጋል።በዚህም መንገድ ለዜጎች ከእጅ ወደ አፍ የሆነ የሥራ ዕድል ሳይሆን ዘላቂና ጥራት ያለው የሥራ ዕድል በመፍጠር አርዓያ እንሆናለን ብለዋል፡፡

ብሔራዊ የሥራ ጉባዔ መንግሥት ሥራ ዕድል ፈጠራን አስመልክቶ ያስቀመጠውን ስትራቴጂካዊ አቅጣጫ ተከትሎ በቀድሞው የሥራ ዕድል ፈጠራ ኮሚሽን በ2012 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘጋጀ ጉባዔ ነው። በዚህም መሠረት ጉባዔው የገበያ ተዋናዮች የሚወያዩበትን፤ ችግሮች ተለይተው የመፍትሄ አማራጮች የሚመላከቱበትን፤ የእርስ በርስ ትስስር የሚፈጥሩበትን

«የሥራ ዕድል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







አርሾ
ARSHO MEDICAL LABORATORIES P.L.C
በትውልድ የታመነ!
አድራሻ- አራት ኪሎ፣
ከአራዳ ክፍለ ከተማ ሕንፃ ጀርባ፣
የ24 ሰዓት አገልግሎት
612
0114-16-70-89
0911-10-18-18


## «የውስጥ ችግራችን ለውጭ ተጋላጭነታችን ግብዓት እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል»

- አቶ ሌንጮ ለታ የኦነግ መስራች

**ዋቅሹም ፍቃዱ**



አዲስ አበባ፡- የውስጥ ችግር በሰፋ ቁጥር ለጠላቶች ሰፊ ዕድል ስለሚፈጥር ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ፖለቲከኛው አቶ ሌንጮ ለታ አመለከቱ።

አቶ ሌንጮ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት፣ ሰሞኑን የአልሸባብ በተሳሳተ ስሌት ኢትዮጵያ በውስጥ ችግሯ ምክንያት ራሷን መከላከል እንደማትችል በማሰብ ከዚህ በፊት ባልተለመደ መልኩ ብዙ ታጣቂዎችና ብዙ ጦር መሣሪያ በመያዝ ድንበር ጥሶ መግባቱ እንደ ቀላል የሚታይ ክስተት አይደለም።

ሱዳንም በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል የተደረገውን ጦርነት እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም የኢትዮጵያን ድንበር ጥሳ ለመግባት ሞክራለች ያሉት አቶ ሌንጮ፤ ከትንኮሳዎች ጀርባ ሌላ ፍላጎት መኖሩ እንዳለ ሆኖ የውስጣችን ችግር አስተዋጽኦ ማድረጉ አያጠያይቅም ብለዋል።

ያም ሆኖ ግን በተለይ በአልሸባብ ላይ የተወሰደው እርምጃ ቡድኑ የሃይማኖት አክራሪነትን ለማስፋትና ሌላውን በመጨፍለቅ ታላቋ ሶማሊያን ለመገንባት የሚደረገውን የቀን ቅዠቱን እንቅስቃሴ እርቃኑን ያስቀረና በተቃራኒው ደግሞ የኢትዮጵያን ጥንካሬ ያስመሰከረ አኩሪ ገድል ነው ያሉት አቶ ሌንጮ፣ ለዘላቂ ድል ግን ብሎም ጠላቶቻችንን ማፈናፈኛ ለማሳጣት ወደ ውስጥ በደንብ መመልከት ተገቢ መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ ዓለም እየተስተዋለ ያለው የሰላም እጦት አሳሳቢ መሆኑ እንዳለ ሆኖ በተለይ በምሥራቅ አፍሪካ በፊት የነበረው በጥርጣሬ የመተያየት ችግር እየሰፋ መጥቷል ያሉት አቶ ሌንጮ፣ በሱዳንም ሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ የጸጥታ ችግር እያለ እንደገና በድንበር ሰበብ መጣላት የዚሁ አንዱ ማሳያ

«የውስጥ ችግራችን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል «

## የሰላም ውይይቱ የኢትዮጵያን ጥቅምና አንድነት ባስከበረ መልኩ መካሄድ እንዳለበት ተጠቆመ

**አስናቀ ፀጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በመንግሥትና በሕወሓት በኩል ለሰላም ሲባል የሚደረገው የሰላም ውይይት የኢትዮጵያን ጥቅም ባስጠበቀና አንድነትን ባስከበረ መልኩ መካሄድ እንዳለበት የቀድሞ የአገሪቱ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች ተናገሩ።

የቀድሞ የአየር ኃይል ጦር አዛዥ ብርጋዴሬ ጄኔራል ተስፋዬ ሀብተማርያም ጦርነት አውዳሚ፣ የሰው ሕይወት ቀጣፊ፣ ኢኮኖሚን የሚያደቅና ለስደት የሚዳርግ መሆኑንና በፍላጎት ሳይሆን በግዳጅ የሚገባበት መሆኑን ገልፀዋል። ከዚህ አኳያ ተቃራኒ ቡድኑ ለድርድሩ ሰላማዊ ሆኖ ከቀረበ የሁለቱ ወገኖች

የሰላም ውይይቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY
ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር


0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565

UNIC ETHIOPIA
ሕብረት ኢንሹራንስ አማ
THE UNITED INSURANCE COMPANY SC
Tomorrows Company Today'
ለህይወት
ህጋዊ ግዴታዎ
ለንብረት
ለሁሉም የመድን ፍላጎትዎ
+251 111 26 34 34
united.insurance@unic-ethiopia.com
7469

ዜና

# የከተማዋን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት የሚያሳድጉና ስሟን የሚመጥኑ ፕሮጀክቶች እየተከናወኑ መሆኑ ተገለጸ

## -የፑሽኪን- ጎተራ ማሳለጫ መንገድ ተመርቋል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የከተማዋን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት የሚያሳድጉና ስሟን የሚመጥኑ ፕሮጀክቶች በመከናወን ላይ መሆናቸውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስታወቀ።የፑሽኪን -ጎተራ ማሳለጫ ዘመናዊ የመንገድ ፕሮጀክት በትናንትናው ዕለት ተመርቋል።

የምርቃ ሥነሥርዓቱ ላይ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ እንደገለጹት፤ የሳርቤት - ጎፋ ማዞርያ - የፑሽኪን -ጎተራ ማሳለጫ ዘመናዊ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ሙሉ ለሙሉ ተጠናቆ ለአገልግሎት መብቃቱ ለከተማዋ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አለው።ይህ ፕሮጀክት የተመረቀው በኢትዮጵያ የትውልድ አሻራ ደምቆ በዓለም አደባባይ ባንፀባረቀበትና አስደናቂ የድል ብስራት በተበሠረበት ማግስት መሆኑ ልዩ ያደርገዋል ብለዋል።

ተስፋ መቁረጥን ተስፋ አስቆርጠን አዳዲስ ፕሮጀክቶችን አጠናቀን እያስመረቅን ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ ለከተማችን ትልቅ ብስራት የሆነው የፑሽኪን -ጎተራ ማሳለጫ ዘመናዊ መንገድ ፕሮጀክት በፈተና ውስጥ ሆነን ለአገልግሎት ክፍት አድርገናል ብለዋል።

ከንቲባዋ እንደገለጹት፤ የከተማችንን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትና ስሟን የሚመጥን ውበት ለማላበስ በርካታ ፕሮጀክቶችን ጀምረን ማጠናቀቅ ችለናል።ከነዚህ ፕሮጀክቶች ውስጥ በመንገድ ዘርፍ ብቻ በዚህ አመት ከፍተኛ በጀት በመበጀት 24 አዳዲስ መንገዶችን በመገንባትና ነባር መንገዶች የአገልግሎት ጊዜያቸው ረዘም ያለ እንዲሆን የጥገና ሥራ ተከናውኗል።

እንደ ከንቲባዋ ገለጻ፤ ከተማ አስተዳደሩ በከተማዋ የተለያዩ ማዕዘናት ከ28 ቢሊዮን ብር በላይ በመመደብ ከሁለት መቶ ሰማንያ ሁለት ኪሎ ሜትር በላይ ርቀትን የሚሸፍኑ የአስፓልት መንገዶችን በማከናወን ሂደት ላይ ይገኛል።ፕሮጀክቶቹ ሲጠናቀቁ ለከተማችን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያና ሁለንታዊ የለውጥ እንቅስቃሴ ትልቅ ሚና ይኖራቸዋል።እንዲሁም አዲስ አበባን ዓለም አቀፍ ገጽታ




ለማላበስ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል።በአጠቃላይ በመንገድ ዘርፍ በሁሉም ቀኖች 24 ሰዓት በመሥራት ጥሩ ውጤት እየተመዘገበ ነው።

የፑሽኪን ጎተራ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት በአንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ወጪ መገንባቱን የገለጹት ከንቲባ አዳነች፤ በውበትም በጥራትም እስካሁን ከተገነቡት የላቀና የከተማዋን ቀጣይ ትልም አመላካች መሆኑን ተናግረዋል።

ፕሮጀክቱ በተያዘለት ጊዜና በጀት በጥራት የተጠናቀቀ መሆኑ የፕሮጀክት መፈጸም አቅማችንን ቀጣይነትና አዳጊነት አመላካች ነው ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ የከተማዋን የትራንስፖርት ችግር ፈቺ አካል የሚሆንና ቀጣይ እድገትን ታሳቢ ያደረገ ከመሆኑም በላይ ቄራንና አካባቢውን ከተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች ጋር በማስተሳሰር ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብለዋል።

ቻይና የኢትዮጵያ እውነተኛ የልማት አጋርና የረጅም አመት ወዳጅ መሆኗን የገለጹት ከንቲባዋ፤ በሁሉም መስክ የጀመርናቸው ፕሮጀክቶች ፍሬ እያፈሩ ለከተማችን ነዋሪዎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ተስፋን እያደሱና ምቹ የመኖሪያ አካባቢ እየሆኑ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

ከንቲባ አዳነች እንዳሉት፤ የዜጎችን የኑሮ ጫና የሚያቃልሉ ሥራዎችን በማስፋፋትና የተሟላ የመሠረተ ልማት ዝርጋታን በተለይ የመኖሪያ ቤት ግንባታን በሰፊው ትፈልጋለች።ይህንን እውን ለማድረግ የከተማ አስተዳደሩ ጠንክሮ እየሠራ ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ሞገስ ጥበቡ በበኩላቸው፤ የፕሮጀክቱ ርዝመት 3ነጥብ 8 ኪሎሜትር መሆኑን ገልፀው ከ30-45 የጎን ስፋት አለው ብለዋል።እንዲሁም 320 ሜትር ርዝመትና 9 ሜትር ስፋት ያለው ዋሻ ያለውና ተሻጋሪ ድልድይ አብሮ የተገነባለት መሆኑንም አስታውቀዋል።

በምረቃ ሥነ ሥርዓቱ ላይ የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስትር ዳግማዊት ሞገስ፣ የገንዘብ ሚኒስትር አሕመድ ሺዴ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ ጃንጥራር አባይ እና የቻይና ኤምባሲ ጉዳይ አስፈጻሚ ሺን ኪንግማን እንዲሁም የመዲናዋ ከፍተኛ አመራሮች ተገኝተዋል።

# የኢንዱስትሪው ቡቃያዎች

**ሞገስ ተስፋ**

ዛሬ ላይ በውስን ሀብት የተጀመረው የፈጠራ ሥራ ነገ ለበርካቶች የሥራ ዕድል የመፍጠር አቅም አለው። በአገራችን ትልልቅ የንግድና ኢንዱስትሪዎችን የሚያንቀሳቅሱ ባለሀብቶችም አብዛኛዎቹ ከአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የጀመሩ ናቸው።

በኢትዮጵያ ካለፉት ወራት ጀምሮ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› ንቅናቄ ማምረት ያቆሙ ፋብሪካዎች እንዲያመርቱ ለማስቻል ሰፊ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። ታዲያ ይህ ንቅናቄ ያነገበው እንቅስቃሴ ከአነስተኛ ኢንተርፕራዞች ጀምሮ እስከ ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች በአቅማቸው ልክ ምርት ማምረት እንዲችሉ ያለመ ነው።

በአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የተጀመረ ምርት የማምረት ሂደት ነገ ግዙፍ ኢንዱስትሪ የመሆን አቅም አላቸው። በሲዳማ ክልል ሀዋሳ የሚገኘው የኦሜጋ ጋርመንት ምክትል ሥራ አስኪያጅ አቶ ፍጹም ብዙነህ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኦሜጋ ጋርመንት በ2010 በ50 ሺ ብር ካፒታል የተመሠረተ ሲሆን፣ አሁን ላይ 2 ነጥብ 4 ሚሊዮን ካፒታል ደርሷል። 62 ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ፈጥሮ እንደ ቁምጣ፣ ‹‹ፓካውት››፣ የደንብ ልበሶችንና የመሳሰሉትን አልባሳት በማምረት ለገበያ እያቀረበ ይገኛል።

ያለው የገበያ እንቅስቃሴ መልካም ቢሆንም አሁን በተፈጠረው ዓለም አቀፍ የገበያ የዋጋ ንረት የግብዓት አቅርቦት የፋይናንስ እጥረት እየፈተናቸው እንደሆነ የጠቆሙት ምክትል ሥራ አስኪያጁ፤ ሥራቸውን በሚገባ አስፋፍቶ ለመሥራት ትልቁ ፈተና እንደገጠማቸው ተናግረዋል።

ሥራቸውን በአራት ማሽን እንደጀመሩ የገለጹት አቶ ፍጹም፤ ኦሜጋ ጨርቃጨርቅ አሁን ላይ 80 የሚጠጉ የስፌት ማሽኖች ያሉት ቢሆንም የፋይናንስ እጥረት መኖሩ ባለው ማሽን ልክ የሰው ኃይል ቀጥሮ በሙሉ አቅም ለመሥራት እንዳልተቻለና ለግብዓት የሚሆን ጥሬ ዕቃ ማቅረብ አዳጋች ሆኗል ብለዋል።

በሁለት ቅርንጫፍ ሱቆች አማካኝነት ምርቶቹን



**አቶ ሔኖክ ኃይለገብርኤል**

ለደንበኞቹ እያከፋፈለ የሚገኘው ኦሜጋ ጨርቃጨርቅ ማህበረሰቡ በአገር ውስጥ ምርት የመተማመኑ ጉዳይ ሰፊ ሥራን የሚጠይቅ ነው ይላሉ። አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ወደ ኢንዱስትሪ እንዲሸጋገሩ የፋይናንስ ብድር እንዲያገኙ በመንግሥት በኩል ቢሠራ ሰፊ ሥራ ዕድል በመፍጠር አገርን መቀየር የሚያስችል አቅም እንዳለ አቶ ፍጹም ገልጸዋል።

በሃያት ሞል የሚገኘውና የገላ ሳሙና ማምረት ሥራ ላይ የተሠማራው አቶ ሔኖክ ኃይለገብርኤል በበኩላቸው እንደሚገልጹት፤ ለ13 ዓመታት በባንክ ሥራ ተቀጥረው ሲሠሩ ነበር። ወደ ሳሙና ማምረት የሥራ ፈጠራ የተሸጋገሩበት ሂደት ደግሞ ልጆቻቸው የሚታጠቡበት ሳሙና በገላቸው ላይ ሽፍታ እየፈጠረ ሲያስቸግራቸው በቤታቸው ውስጥ ሳሙና ለማዘጋጀት እንደተነሳሱ ይገልጻሉ።

ለሦስት አመታት በቤት ውስጥ ለቤተሰብ የገላ ሳሙና በማምረት ሥራ የጀመሩት አቶ ሄኖክ ወደ ሥራ ዕድል ለመቀየር ወጥነው በጥናትና ምርምር በመደገፍ በ20 ሺ ብር ካፒታል ወደ ሥራ የገቡ ሲሆን፣ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ 150 ሺ ብር ካፒታል መድረሳቸውን ተናግረዋል።

አሁን ድረስ በገበያው ላይ ገላን ከመታጠብ ያለፈ ጥራት ያለው ለሰውነት ቆዳ ተስማሚ የሆነ የገላ ሳሙና አቅርቦት ችግር እንዳለ መረዳታቸውን የገለጹት ሥራ ፈጣሪው፤ ችግሩን ለመቅረፍ በመሥራታቸው ሳሙናው ተቀባይነት እያገኘ ነው ብለዋል።

አቶ ሄኖክ እንደሚሉት፤ አሁን ባለው የገበያ ሥርዓት የግብዓት አቅርቦት እጥረት፣ የመሥሪያ ቦታ ሼድ አለመኖር፣ የውሃና የመብራት እጥረት ትልቅ ፈተና ሆኖባቸዋል። ይሁን እንጂ ሳሙናው የያዘውን የምርት ጥራት አስጠብቆ ለመዝለቅ በትኩረት እየሠሩ ነው።

የንጽህና መጠበቂያ ምርቶች ሸማቹንና አምራቹን የሚያገናኝ ድልድይ ከተፈጠረ የገበያ ችግር የለባቸውም፤ በቀጣይም የገበያ ችግር ይገጥመናል ብለን አንሰጋም፤ የምርቱ ፍላጎት እስካለ ድረስ ገበያው ይኖራል። አምራቹ ዘርፍ እያደገ በመጣ ቁጥር የሥራ ዕድል የመፍጠር አቅሙም እየጨመረ ይመጣል ሲሉም ተናግረዋል።

‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› የሚለው ንቅናቄ ጥሩ ነው የሚሉት አቶ ሄኖክ፤ ኢንተርፕራይዞችን ከመደገፍ አኳያ ያለው አፈጻጸም ታች ወርዶ በመተግበር ረገድ ያሉ ክፍተቶ መፈታት አለባቸው ብለዋል። ደንበኞችን ለማገልገል የሚቀመጡ አካላት ከላይ በከፍተኛ አመራር ደረጃ የሚሰጡ መረጃዎችና ከታች ፈጻሚዎች ላይ ያለው ሥራ ሊገናኝ እንደሚገባ ገልጸዋል።

ቀጣይነት ያለውና አገርን የሚያኮራ ኢንዱስትሪ ለመገንባት ትልቅ ዕራይ ሰንቀው እየሠሩ መሆናቸውን የተናገሩት አቶ ሄኖክ፤ ለዚህም በጥራት ላይ ሳይደራደሩ አገር የምትኮራበት ምርት ለማምረት እንሠራለን። ሕዝቡ የተዛባውን በውጭ ምርት መተማመን አስተሳሰብ በአገር ውስጥ ምርት እንዲኮራ ለማድረግ ሰፊ ሥራ እየተሠራ ሲሆን የ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ›› ግብ እንዲመታ በየደረጃው ያለው አመራር በቅንጅት ሊሠራ እንደሚገባ አቶ ሄኖክ ጠቁመዋል።

# ከፍተኛ ትምህርት የመውጫ ፈተና ማስፈጸሚያ መመሪያ ጸደቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የከፍተኛ ትምህርትን አገራዊ ቅድመ ምረቃ የመውጫ ፈተናን በአግባቡ ለመምራትና ለማስተዳደር የተዘጋጀው የከፍተኛ ትምህርት መውጫ ፈተና ማስፈጸሚያ መመሪያ ጸደቀ።

የትምህርት ሚኒስቴር ይፋ ባደረገው መረጃ መሠረት፤ መመሪያው በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ እና ጸድቆ ለትግበራም ይፋ ሆኗል።

መመሪያው በመውጫ ፈተና ዝግጅት ሊካተቱ ስለሚገባቸው አገራዊ ዝቅተኛ የትምህርት ብቃት መመዘኛዎችን፣ የሙያ ሥነምግባር ደንቦችን እና ተቋማት ሊከተሏቸው የሚገቡ የአሠራር ሥነ-ሥርዓቶችን ያካተተ መሆኑን ትምህርት ሚኒስቴር አስታውቋል።

መመሪያው የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅና አገሪቱ የምትፈልገውን የሠለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት ከሚደረጉ ማስፈጸሚያ ስልቶች አንዱ መሆኑን ተጠቁሟል።

በመመሪያው ዝግጅት ሂደት ውስጥ በሥርዓተ ትምህርት እና ፈተና ዝግጅት ከፍተኛ ልምድ ያካበቱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምሁራን፣ የሙያ ማኅበራት ተወካዮች እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላት አስፈላጊውን ግብዓት መስጠታቸው ተገልጿል።

የጸደቀው መመሪያ ከሚቀጥለው የትምህርት ዘመን ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን ለሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መላኩን ትምህርት ሚኒስቴር አስታውቋል።

ከዚህ ቀደም ከሁሉም የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች የሚመረቁ ተማሪዎች በሰለጠኑባቸውና በተማሩባቸው ሙያዎች ብቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የመውጫ ፈተና እንዲወስዱ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን የትምህርት ሚኒስቴር ማሳወቁ የሚታወስ ነው።

በጉዳዩ ዙሪያ የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች የምክክር መድረክ ተዘጋጅቶ ውይይት መደረጉንና የመውጫ ፈተናው አስፈላጊነት፣ የፈተና አወጣጥና አፈታት እንዲሁም ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ሰፊ ምክክር ሲደረግ መቆየቱን የትምህርት ሚኒስቴር መረጃ አመልክቷል።

ትምህርት ሚኒስቴር በመጪዎቹ አምስት ዓመታት የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል ጠንካራ ትግበራና ርምጃዎችን እንደሚወስድ ገልጾ፤ በነዚሁ ዓመታት አዲስ የመንግሥት ዩኒቨርሲቲ ከመገንባት ይልቅ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አቅምና ጥራት ማሻሻል ላይ በትኩረት እንደሚሠራ ማሳወቁ የሚታወስ ነው።



ዶክተር አብዱልወሀብ አደም

# በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኘው የዳያስፖራ ማህበረሰብ በኢንቨስትመንት ዘርፍ ተሳትፎ እያደረገ መሆኑ ተገለጸ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኙ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ማህበረሰብ አባላት የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ብልጽግና እውን ለማድረግ በኢንቨስትመንት ዘርፍ ከፍተኛ ተሳትፎ እያደረጉ መሆኑ ተገለጸ።

በአቡዳቢ የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ ቦርድ አባል ዶክተር አብዱልወሀብ አደም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኙ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ማህበረሰብ የዜጎችን መብት ከማስጠበቅ፣ የአገርን ገጽታ ከማስተዋወቅ፣ የክህሎት ሽግግር ከማድረግ ባለፈ በኢንቨስትመንቱ ዘርፍ በመሳተፍ የአገሪቷን ብልጽግና እውን ለማድረግ በትኩረት እየሠራ ነው።

ዳያስፖራው ያለውን ሀብት ተጠቅሞ የኅብረተሰቡን ፍላጎት ያማከለ ሥራ ለማከናወን ዝግጁ መሆኑን የገለጹት ዶክተር አብዱልወሀብ፤ በመሆኑም አስፈላጊውን ሕጋዊ መንገድ በመከተል ኢንቨስት ለማድረግ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እየተደረገ እንዳለ አመላክተዋል።

እንደ ዶክተር አብዱልወሀብ ገለጻ፤ በመካከለኛው ምሥራቅ አገራት የሚገኙ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ማህበረሰብ የአገሪቱን የረጅም ጊዜ የመበልጸግ ምኞት ለማረጋገጥ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርጉ ቆይተዋል።የዳያስፖራው ማህበረሰብ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ዘመቻን በመታገል፣ ለአገር መከላከያ ሰራዊት ገንዘብ በማገዝ እና የማገገሚያ ሂደቱን በማካሄድ ሰፊ ሥራዎችን አከናውነዋል።በቅርቡም በጦርነት ጉዳት ለደረሰባቸው ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአብርሆት ቤተመጻሕፍት በኩል መጽሐፍትን አበርክተዋል።

ከአገር ከወጡ ከ15ዓመት በላይ እንደሆናቸው የሚናገሩት ዶክተር አብዱልወሀብ፤ በተለያየ ጊዜ ወደ አገር ቤት ሲመላለሱ እንደቆዩና በዚህ ጊዜ ውስጥም ኢትዮጵያ እየተለወጠች መምጣቷን ተናግረዋል።ኢትዮጵያ ብዙ ፈተናዎች ቢገጥማትም በተለይ ባለፉት ሦስት ዓመታት አስደናቂ ውጤት እያስመዘገበች እንደምትገኝ መስክረዋል።እንደ እንጦጦ እና ወዳጅነት አደባባይ ያሉ የመዝናኛና የአረንጓዴ ልማት አካባቢ ግንባታዎች አበረታች መሆናቸውን ጠቅሰዋል።በተጨማሪም በሂደት ላይ ያለውን የበጋ የስንዴ መስኖ ምርትና አትክልት የልማት ሥራዎችን አድንቀዋል።

አገሪቱ በአሸባሪው የሕወሓት ጥቃት መጎዳቷን በመጥቀስ በመልሶ ግንባታ ሥራ ላይ የዳያስፖራው ማህበረሰብ ተሳታፊ እንደሚሆን አረጋግጠዋል። በሰሜኑ ግጭት በአሸባሪው ቡድን ንብረት የተዘረፉ፣ የወደሙባቸው ብዙ ትምህርት ቤቶች፣ ኮሌጆች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ሆስፒታሎች፣ ቤተክርስትያኖች፣ መስጊዶች በመኖራቸው ከዳያስፖራው ማህበረሰብ የሚጠበቀውን ለመደገፍ የተጠናከረ ሥራ ይሠራል ብለዋል።

የመካከለኛው ምሥራቅ ኢትዮጵያውያን ዳያስፖራዎች ወደ አገር ውስጥ ከሚላከው ገንዘብ ውስጥ ከ50 በመቶ በላይ የሚሆነው ከፍተኛ አቅም በማበርከት ላይ እንዳለ ጠቁመው፤ ይህንኑ በማጠናከር በመልሶ ግንባታ ሥራ ላይ ከመሳተፍ ባሻገር ኮሙኒቲው ተቀማጭ ከሆነው ሀብቱ ትልቅ የኢንቨስትመንት ሥራ ለመሥራት

# በአረንጓዴ አሻራው 25 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን መሳተፋቸው ተገለጸ

**ጌትነት ተስፋማርያም**



ፎቶ፡- ዳኜ አበራ

አዲስ አበባ፡- በአረንጓዴ አሻራ ሥራዎች ከችግኝ ማፍላት እስከ እንክብካቤው 25 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን መሳተፋቸውን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የአራት ዓመታቱ የአረንጓዴ አሻራ ዘመቻ መጠናቀቅን አስመልክተው ባወጡት መግለጫ እንደገለጹት፤ 25 ሚሊዮን ዜጎች ችግኝ በማፍላት፣ የችግኝ ጉድጓድ በመቆፈር እና የተተከለውን በመንከባከብ ተሳትፎ አድርገዋል።

ለአራት ተከታታይ ዓመታት በኢትዮጵያ ሲካሄድ የቆየው የአረንጓዴ አሻራ ዘመቻ በአገሪቱ አረንጓዴ ባህልን በመፍጠር ስኬታማ መሆኑን ገልጸዋል።

የከተሞቿን የአረንጓዴ ሽፋን ለማሳደግ የአረንጓዴ አሻራ ዘመቻን መጀመሯን አስታውሰው፤ ለአራት ዓመት በቆየው ዘመቻ 20 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ወጥና ብትነሳም፤ ዜጎቿ 25 ቢሊዮን ችግኞችን በመትከል ካስቀመጡት ግብ በላይ መፈፀማቸውን ነው የጠቆሙት።

የአረንጓዴ አሻራ ዘመቻው ሲጀመር 40 ሺህ ብቻ የነበሩት የችግኝ ማፍያዎች አሁን ላይ ወደ 121 ሺህ ማደጋቸውንና በዓመት ሰባት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ችግኝ የማፍላት አቅም ላይ መደረሱን ዘርዝረዋል።

አረንጓዴ ባህልን ከመፍጠር ባለፈ ዘመቻው ለ767 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ያበረከተውን ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅኦም አመልክተዋል።

ከዚህ ባለፈ ለችግኝ ተከላ የሚያስፈልጉ ቦታዎችን በመምረጡ እና ለተከላ በማዘጋጀቱ ረገድም የታየው ውጤት አበረታች መሆኑንም ጠቁመዋል።

በመላው አገሪቱ የሚገኙ ከተሞች አሁን ላይ የአረንጓዴ ስፍራ አስፈላጊነትን ተረድተው ቦታ እያዘጋጁለት መምጣታቸው ለተፈጠረው አረንጓዴ ባህል ማሳያ መሆኑን አስረድተዋል።

የአረንጓዴ አሻራ ባህል ለቀጣዩ ትውልድም የሚቆይ መሆኑንም አንስተው፤ በዚህ ስኬት ውስጥ የፖለቲካ ፍላጎት እና ቁርጠኝነት ቁልፍ ሚና መጫወቱንም ነው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የገለፁት።

በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብሩ በርካቶች መሳተፋቸውን ያደነቁት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ አሁንም ብዙ ሥራ የሚጠበቅብን ቢሆንም ንቅናቄው በአገሪቱ ውጤት እንዳፈራ ግን ጥርጥር የለንም ሲሉ በመግለጫቸው አመላክተዋል።

ያለፉትን ጥቂት ሳምንታት ብቻ በዓለም ዙሪያ የተስተዋሉት የጎርፍ አደጋ፣ የደን ቃጠሎ፣ ኃይለኛ ማዕበል እና ያልተለመደ ሙቀትን የመሰሉ ሁኔታዎች ለዓየር ንብረት ለውጥ ዓይነተኛ ማሳያዎች መሆናቸውን ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመልዕክታቸው አንስተዋል።

የአፍሪካ ቀንድ ያስተናገደው ድርቅ የዚሁ የዓየር ንብረት ለውጥ ውጤት መሆኑንም ጠቁመው፤ በኢትዮጵያም የዓየር ንብረት ለውጥ የውሃ ምንጮችን አድርቋል፤ በአንዳንድ የአገሪቱ ክፍሎችም የድርቅ አደጋን ማስከተሉን ገልጸዋል።

አሁን ላይ ዓለም እየተሰቃየ ያለበትን ይህን ችግር ለመፍታት ከስብሰባዎች ያለፈ ተግባራዊ መፍትሄ መውሰድ ያስፈልጋል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ መክረዋል።

የታዳሽ ኃይል በሆኑት የውሃ፣ ንፋስ፣ ፀሐይ እና የእንፋሎት የኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ላይ የምታውለው መዋዕለ ንዋይ ሌላው የዓለም አየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል በበኩሏ እየተወጣች የምትገኘው ኃላፊነት መሆኑን ነው በጠቅላይ ሚኒስትሩ መልዕክት የተብራራው።

አሁንም ብዙ ሥራ ቢጠበቅም በአገሪቱ አረንጓዴ ባህልን በመፍጠሩ ረገድ ዘመቻው እንደተሳካ ጥርጥር የለንም ብለዋል።

አፍሪካ ብሎም ዓለም ተፅዕኖው እየከፋ የመጣውን የዓየር ንብረት ለውጥ ለመከላከል ልክ እንደኢትዮጵያ ተግባራዊ የአረንጓዴ አሻራን በመፍትሄነት ሊጠቀሙ እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።

# ግድቡ በተፋሰሱ አገራት ላይ ጉዳት እንደማያደርስ ማረጋገጡን የደቡብ ሱዳን ልዑክ ገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በተፋሰሱ አገራት ምንም ዓይነት ጉዳት እንደማያደርስ አረጋግጠናል ሲሉ የደቡብ ሱዳን ፕሬዚዳንት የብሔራዊ ደኅንነት ጉዳዮች አማካሪ ኮንግ ቲፕቲፕ ጋትሏክ ገለጹ።የመከላከያ ሚኒስትርና የታላቁ ኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የቦርድ ሰብሳቢ ዶክተር አብርሃም በላይ፤ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካውያንም የጋራ የልማት ፕሮጀክት ነው ብለዋል።

በኢትዮጵያ የሦስት ቀናት የሥራ ጉብኝት እያደረገ የሚገኘው የደቡብ ሱዳን የደኅንነትና ሲቪል ሹማምንት ከፍተኛ ልዑካን ቡድን ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ጎብኝተዋል።

የደቡብ ሱዳን ፕሬዚዳንት የብሔራዊ ደኅንነት ጉዳዮች አማካሪ ኮንግ ቲፕቲፕ ጋትሏክ ለኢዜአ እንዳሉት፤ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የተፋሰሱ አገራት ጭምር የልማት ፕሮጀክት ነው።

ከኢትዮጵያ መንግሥት በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ለጉብኝት መምጣታቸውን የገለጹት የፕሬዚዳንቱ የደኅንነት ከፍተኛ አማካሪ፤ በጉብኝታቸውም የህዳሴ ግድብ ጎረቤት አገራትን በኃይል የሚያስተሳስር ፕሮጀክት መሆኑን አረጋግጠናል ብለዋል።

በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ዙሪያ የሚነሱ ጉዳዮች በድርድር መፈታት እንዳለባቸው ገልጸው፤ ባደረግነው ጉብኝትም ግድቡ የጋራ የልማት ፕሮጀክት እንጂ ምንም ዓይነት ችግር የለውም ብለዋል።

ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ለመጎብኘት የመጣነው ከኢትዮጵያ መንግሥት በቀረበልን ጥሪ መሠረት ነው ያሉት ኮንግ ቲፕቲፕ በዚህ መሠረት ግድቡን ስንጎበኝ ያረጋገጥነው ነገር የጎረቤት አገራትን በኤሌክትሪክ ኃይል ሊያስተሳስር እንደሚችል ነው ብለዋል።

«ምክንያቱም ግድቡ የልማት ፕሮጀክት ነው።በግድቡ ዙሪያ ያሉ ጉዳዮች በድርድር መፈታት አለባቸው።እኛም የመጣነው የሁለቱን አገራት ግንኙነት ለማጠናከር



ነው።ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ምንም ዓይነት ችግር እንደሌለው በጉብኝታችን አረጋግጠናል» ሲሉም ተናግረዋል።

የኢፌዴሪ የመከላከያ ሚኒስትርና ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ዶክተር አብርሃም በላይ፤ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካውያን በተለይም ለጎረቤት አገራት የጋራ የልማት ፕሮጀክት ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ፣ ለሱዳንና ጂቡቲ ኤሌክትሪክ ኃይል ማቅረብ ጀምራለች፤ ለኬንያ በቅርቡ መላክ እንጀምራለን፤ ደቡብ ሱዳንም የኃይል እጥረት ስላለባት ፍላጎት ካላት እንሰጣለን ብለዋል።

በመሆኑም ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በኢትዮጵያውያን ብርቱ መስዋዕትነት እየተገባደደ ያለ ፕሮጀክት ቢሆንም የተፋሰሱን አገራት ጭምር ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑን ገልጸዋል።

በግድቡ ግንባታ ሂደት የታችኛው ተፋሰስ አገራትን ታሳቢ በማድረግ ሁለት ዓመቱን ሙሉ ውሃ የሚፈስባቸው ሁለት የውሃ ማስተላለፊያ ሰፋፊ ቱቦዎች እንዲኖሩ አድርገናል ሲሉም ተናግረዋል።

የታችኛው ተፋሰስ አገራት ወንድሞቻችን የግድቡ ግንባታ በውጭ ሆነው የሚያወሩትና በተግባር ያለው የተለያየ በመሆኑ የጋራ የልማት ፕሮጀክታችን እንደሆነ ይረዱናል ብለዋል ዶክተር አብርሃም።

የኢትዮጵያ የውስጥና የውጭ ጠላቶች የሲሚንቶ ፋብሪካዎች እንዳይሠሩ፣ ከውጭ የሚገቡ ግብዓቶች እንዳይገቡ እንዲሁም አስፈላጊ ግብዓቶች እንዳይቀርቡ ክልከላ ሲያደርጉ እንደነበርም ጠቅሰዋል።

የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጄነራል ተመስገን ጥሩነህ፤ ታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ በውስጥ ባንዳዎችና በውጭ ጠላቶች የተለያዩ ጥቃት እንዲደርስበት ሲደገስለት ነበር ብለዋል።

ሕዝቡ ሲፈነዳና ሲተኮስ አላየም እንጂ ሀብታችንን እንዳንጠቀም በተላላኪ ባንዳዎች የሚላኩ ከመፈንዳታቸው በፊት በርካታ ፈንጂዎችን አክሽፈናል፤ ወደፊትም ግድቡን ለመጠበቅ እንቅልፍ አይኖረንም ብለዋል።

የህዳሴው ግድብ ግንባታ አፍሪካውያን የራሳቸውን ሀብት በራሳቸው አቅም መጠቀም እንደሚችሉ ያሳየ መሆኑንም ዳይሬክተር ጄነራሉ ገልጸዋል።

የጎረቤት አገራት ኢትዮጵያ የውሃ ማማ መሆኗን በመረዳት በአረንጓዴ ዐሻራ ችግኝ በመትከል ሌሎች ዓባዮችን መፍጠር እንዲችሉ ጥሪ መቅረቡንም ጠቅሰዋል።

የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሦስተኛ ዙር የውሃ ሙሌት በስኬት መጠናቀቁና የሁለተኛው ተርባይን ኃይል ማመንጨት መጀመሩን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ማብሰራቸው ይታወቃል።

# «ሰራዊቱ ዘመኑ ያፈራቸውን ወታደራዊ ቴክኖሎጂዎችን እንዲታጠቅ ጥረት ይደረጋል»

**-ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ**

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በ2015 በጀት ዓመት ሰራዊቱ ዘመኑ ያፈራቸውን ወታደራዊ ቴክኖሎጂዎችን እንዲታጠቅ ጥረት ይደረጋል ሲሉ የኢፌዴሪ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ተናገሩ።

የመከላከያ ሎጂስቲክስ ዋና መምሪያ ከዕዝ የሎጂስቲክስ አመራሮች ጋር ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀምን በመገምገም ለጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማጆር ሹሙ ገለፃ ባቀረበበት ወቅት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ እንደተናገሩት፤ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ዘመኑ ያፈራቸውን ወታደራዊ ቴክኖሎጂዎች እንዲኖሩት ጥረት ይደረጋል።

በ2015 በጀት ዓመት ለሰራዊታችን የተሟላ ሎጂስቲክስ በማቅረብ አስተማማኝ ወታደራዊ ኃይል ለመገንባት እየሠራን ነው ሲሉ ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ




ገልጸዋል።

የሎጀስቲክስ አቅርቦት የሰራዊቱ የጀርባ አጥንት መሆኑን የጠቀሱት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ፣ በሁሉም አቅጣጫ የውስጥ እና የውጭ ጠላቶቻችን ግንባር ፈጥረው ቢሰለፉም ለሰራዊታችን የተቀናጀ ሎጂስቲካዊ ፍላጎቶችን በማቅረብ ከሰራዊቱ ጀግንነት ጋር ተዳምሮ ጠላትን ማሳፈር ችለናል ብለዋል።

የሎጂስቲክስ አሠራር እና ሥርዓት በሚፈቅደው ልክ ሰራዊቱ በሚያስፈልገው ቦታ እና ሰዓት የሚያስፈልገውን ሁሉ በማቅረብ ሎጂስቲክስ የሰራዊቱ ደጀን መሆኑን ጠቁመዋል።

አገር ውስጥም ሆነ በሰላም ማስከበር ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ መከላከያ አስፈላጊውን የሎጀስቲክስ አቅርቦትና ቴክኖሎጂ እንዲኖረው ያልተቋረጠ ድጋፍ እንደሚደረግ አስታውቀው፤ ከከፍተኛ አመራር እስከ እግረኛው ተዋጊ ድረስ በወታደራዊ ሳይንስና ጥበብ መምራት በሚያስችል ደረጃ ሰፋፊ ስልጠናዎች መሰጠቱንም ጠቁመዋል።

ከዚህ ባለፈ በቀጣይ ጊዜያትም ሰራዊቱ በአካልና በአዕምሮ ብቃቱ የተጠናከረ እንዲሆን የተለያዩ ስልጠናዎች እንደሚሰጡ ተናግረዋል።

በአሁኑ ሰዓት የሠራዊቱን የውጊያ ብቃት በማሳደግ በአገራችን ላይ ሊቃጣ የሚችል ማንኛውንም አደጋ መመከት የሚያስችል ቁመና ላይ እንገኛለን ሲሉም ተናግረዋል።

ሰራዊቱን በሰው ኃይል፣ በትጥቅ እና በስነ-ልቦና የማዘጋጀትና የማዘመን ሥራዎች በትኩረት እየተሠሩ ነው፤ ጥንካሬዎቻችንን በማጎልበት ተልዕኮ የመፈፀም ብቃት ከፍተኛ ደረጃ መድረሱን የመከላከያ ሰራዊት አስታውቋል።

የመከላከያ ሎጀስቲክስ ዋና መምሪያ ኃላፊ ሌተናል ጀኔራል አብዱራህማን እስማኤል በበኩላቸው፤ የሎጂስቲክስ ዝግጁነት ከመቼውም ጊዜ በላይ ያደገ መሆኑን መግለጻቸውን ከአገር መከላከያ ሠራዊት የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

# የሰላም ውይይቱ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ቁርሾ በሰላም ማለቁ ተገቢ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ከአቅም በላይ የሆኑ ግዴታዎች ለውይይት የሚቀርቡ ከሆነ ግን ተገቢ እንዳልሆኑና አገርን አሳልፎ በመስጠት ሰላም ሊኖር እንደማይችልም አስታውቀዋል።

ሁለቱም ቡድኖች ሰላም ፈላጊዎች መሆን እንደሚጠበቅባቸው የገለፁት ብርጋዴሬ ጄኔራል ተስፋዬ ሀብተማርያም፤ ለሰላም፣ ለጥሩ መንፈስና ለእውነት ከቆሙ ድርድሩን ማካሄዱ ተገቢ መሆኑን ጠቁመዋል። የአንዱን መብት አሳጥቶ የሌላኛውን መብት ለመገንባት ከሆነ ግን የሰላም ንግግር ትርጉም አልባ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የቀድሞ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ሌፍተናንት ጄነራል አዲስ ተድላ በበኩላቸው በመንግሥትና በሕወሓት በኩል በሰላም ጉዳይ የሚደረገው የሰላም ውይይት በመሠረታዊነት የኢትዮጵያን አንድነት ባስከበረ መልኩ መሆን እንደሚገባው አመልክተዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ውይይቱን ለማስኬድ በሕወሓት በኩል በብሔር ከፋፍሎ የመግዛት



ብ/ጄኔራል ተስፋዬ ሃብተማርያም



ሌ/ጄኔራል አዲስ ተድላ

እሳቤና ታላቋ ትግራይ የሚባለው ጉዳይ እንደማይሠራና ከዚህ አንፃር ሕገመንግሥቱ ሊሻሻል እንደሚገባም ጠቁመዋል። ሕገመንግሥቱ የሁሉንም ኅብረተሰብ ፍላጎት የያዘ እንጂ የሕወሓትን የግል ጥቅም የሚጠበቅ መሆን እንደማይገባውም አስታውቀዋል።

በነዚህ ቅድመሁኔታዎች ሁለቱ ኃይሎች ተስማምተው ወደሰላም ካመሩ ግን መልካም መሆኑን ሌ/ጄኔራል አዲስ ተናግረዋል።

# «የውስጥ ችግራችን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መሆኑንና መዘዙ ከባድ እንደሆነም አመላክተዋል።

በታላቁ ህዳሴ ግድብ ምክንያት ግብጽና ሱዳን ሌሎች አገራት ኢትዮጵያን በጥርጣሬ እንዲያዩ አልፎም ኢትዮጵያ እንዳትረጋጋ በውስጥ ጉዳይዋ የሚያሴሩት የሴራ እንቅስቃሴ ቀላል እንዳልሆነ የጠቆሙት ፖለቲከኛው፣ ግድቡ ብዙ ዛቻዎችን በማለፍ ለፍሬ መብቃቱ የሕዝቡ አንድነት ውጤት ነው ብለዋል። በመሆኑም ከሁሉም በላይ የውስጥ አንድነት ማጠናከር ተቀዳሚ ተግባር ማድረግ እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

ከሁሉም በላይ ግን ሦስተኛ ዙር የውሃ ሙሌት በስኬት በመጠናቀቁ በግድቡ ላይ የሚታቀድ ማንኛውም ሴራ ከኢትዮጵያ ይልቅ የታችኛውን ተፋሰስ አገራት በእጅጉ ስለሚጎዳ ከዚህ በኋላ የግድቡ ደህንነት የጋራ ጉዳይ መሆኑ ትልቅ ድል መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ አቶ ሌንጮ ማብራሪያ፣ ኢትዮጵያ በመልካ ምድር አቀማመጧ በቀይ ባህር አካባቢ ስለምትገኝ ጠላቶቿ ከግብጽና ከሱዳን በላይ ነው። የግድቡ ግንባታ ቢጠናቀቅ እንኳ የጠላቶች ሴራ አይቆምም። በእርግጥ ከዚህ በኋላ ለመኖር ሲሉ ለህዳሴ ግድብ ደህንነት የሚጨነቁ የታችኛው ተፋሰስ አገራት ናቸው። ሆኖም አቅጣጫ በመቀየር ሴራዎችን ከማድረግ ወደኋላ አይሉም። የሕዝቡ አንድነት ከተጠናከረ የጠላቶች ሴራ ከንቱ ሆኖ ይቀራል።

የጠላቶችን ትልም ለማምከን ብሎም ኢትዮጵያን የልማትና የዴሞክራሲ ተምሳሌት ለማድረግ ብቸኛው አማራጭ ዴሞክራሲያዊ የሆነ ሕብረ ብሔራዊ ፌዴራሊዝምን ማስፈን መሆኑን ያላቸውን እምነት የተናገሩት አቶ ሌንጮ፣ ለእሳቸው ሌሎች አማራጮች አገሪቱን ወደ ለየለት ቀውስ የሚያመሩ ናቸው። ያም ሆኖ ግን ጉዳዩ በጥቂት ግለሰቦች የሚወሰን ጉዳይ በመሆኑ የትኛው የመንግሥት አወቃቀር እንደሚያዋጣ ለሕዝብ ማቅረብ ያስፈልጋል ብለዋል።

ባለፉት 27 ዓመታት ዴሞክራሲያዊ ያልሆነው ሕብረብሔራዊ ፌዴራሊዝም አገሪቱ ዛሬ ለገባችበት ችግር አንዱና ዋነኛው ምክንያት ነው ያሉት አቶ ሌንጮ፣ ከዚህ አንጻር የበላይነትን ለምደው እኩልነት የማይጥማቸው አካላት መኖራቸው ግልጽ ነው ብለዋል። ሆኖም ብዙኃኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎት ማገልገል ከተቻለ ቀሪውን በሂደት መቅረፍ እንደሚቻል አስገንዝበዋል።

# «ዘላቂና ጥራት ያለው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ዕድል በመፍጠር የሥራ ዕድል ፈጠራ አጀንዳነት ትኩረት እንዲሰጠው ማስቻልን ዓላማ ያደረገ ነው።

እንደአገር የሥራ ገበያው ለሚገፈልገው የሰው ኃይል ብቁና ተወዳዳሪ አድርገን ማቅረብ መቻላችንን ማረጋገጥ ይኖርብናል ያሉት ወይዘሮ ሙፈሪያት፤ ይህ ለጀመርነው አገራዊ ለውጥ ትልቅ ትርጉም አለው ብለዋል። ገበያው ምን ይፈልጋል የሚለውን መርምሮ ሥልጠናዎችን ከማዘጋጀት አንፃር እንደመጀመሪያ ምዕራፍ ጥሩ ርቀት ሄደናልም ሲሉ አክለዋል።

የሥራ ገበያውን ለማጣጣም ከባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ ዕቅድ ተነድፎ ጅምር ሥራዎች እንደተሠሩ ገልፀው፤ ሥራዎችም የሙያ ደህንነትና ጤንነትን ታሳቢ ያደረጉና በዘላቂነትም የኢንዱስትሪ ሰላምን ሊያመጡ የሚችሉ እንዲሆኑ ተደርጎ ይሠራል ብለዋል። በዚህም በአገር ውስጥ እና በአፍሪካ ብሎም በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ የሥራ ዕድሎችን ለመጠቀም የሚያስችሉ አቅጣጫዎች መቀመጣቸውን ጠቁመዋል።

ዓለም ላይ በቀጣይ ዓመታት 10 ሚሊዮን ዜጎችን የሚፈልግ የሥራ ገበያ አለ ያሉት ሚኒስትሯ፤ በአፍሪካም እንዲሁ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የሥራ ገበያዎች እንደሚኖሩ አብራርተዋል። ስለዚህም በአገር ውስጥ በአፍሪካና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ የሥራ ዕድሎችን ለመጠቀም የሚያስችል በቂ ዝግጅት ይደረጋል። እነዚህ ዝግጅቶችም ተዳምረው ለዜጎች ከእጅ ወደአፍ የሥራ ዕድል ሳይሆን ዘላቂና ጥራት ያላቸው የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር ያስችላሉ ሲሉ ጠቁመዋል።

እንደ ወይዘሮ ሙፈሪያት ገለፃ፤ በአገራችን ሥራ በርካታ ማነቆዎች አሉት። እነዚህን ማነቆዎች አቅማችንን በማሰባሰብ ለመፍታት የሚያስችለንን ቁመና ይዘናል። ተቋሙ ለዚህ ይረዳው ዘንድ ክሂሎት፣ የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የኢንዱስትሪ ሰላም የተባሉ ሦስት ምሰሶዎችን ማዕከል አድርጎ ተቋቁሟል። እነዚህ ምሰሶዎች መዋቅራዊ የሆኑ የሥራ ችግሮችን መፍታት ይችላሉ ተብሎ የታመነባቸው ናቸው።

ከሥራ ባህል፣ ከታታሪነት እና ከፈጠራ ጋር የሚያያዙ ሊፈቱ የሚገባቸው በርካታ ጉዳዮች እንዳሉም አንስተዋል። ክሂሎት ሲባል በእጅ ተነክቶ ስለሚሠራ ነገር ብቻ መታሰብ የለበትም፤ አእምሮ ላይም መሥራት የሚጠይቁ በርካታ ጉዳዮች አሉም ብለዋል።

እንደ ሚኒስትሯ ገለፃ፤ ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ያላቸውን ሀብት አውጥተው ለሥራ ዕድል ምቹ ሁኔታ እንዲፈጥሩ ይጠበቃል። ሠልጣኞችም በሥልጠና ቆይታቸው የሥራውን ዓለም ለመቀላቀል የሚያስችላቸው ብቁ ዝግጅት እያደረጉ የሚቆዩበት ወቅት እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል አዲስ አቅጣጫ ተይዟል። ይህ የሥራን ማነቆዎችን ለመፍታት መሠረታዊ ለውጥ ያመጣሉ ተብለው ከሚጠበቁ እንኳር ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ነው።

በ2014 በጀት ዓመት የ3 ነጥብ 2 ሚሊዮን የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ 2 ነጥብ 7 ሚሊዮን የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሉን የሥራና ክሂሎት ሚኒስትሯ ገልፀዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## “ወሳሂ እኛ ግብጽን አንጎዳም!”

በተለያዩ ዘመናት የነበሩ የግብጽ መንግስታት የዓባይን ወንዝ ውሃ በተመለከተ ባሰራጨቻው የተሳሳቱ መረጃዎች የግብጽ ህዝብ ባልተገባ ስጋት ውስጥ እንዲኖር ሆኗል። በተለይም እኤአ ከ1960ዎቹ ጀምሮ ሁኔታዎች መልካቸውን እየቀየሩ የወንዙ ውሀ የሀገር ውስጥ ፖለቲካ መዘወሪያ አቅም የማድረግ የፖለቲካ ሴራ ተጠናክሮ ቀጥሏል።

ይህ የግብጽን ህዝብ ያልተገባ ስጋት ውስጥ በመጨመር በህዝቡ ስጋት የመቆመር ፖለቲካ ሴራ በሁለቱ ሀገራት ህዝቦች መካከል የቆየውን የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት በየዘመኑ በጥርጣሬና ባለመተማማን ውስጥ እንዲወድቅ ቢያደርገውም ከዚህ ባለፈ በተጨባጭ በግብጽ ህዝብ ላይ የፈጠረው ችግር ሆነ ተግዳሮት የለም ።

ዓባይ ወንዝ ለኢትዮጵውያንም ሆነ ለግብፃውያን ከዛም በባለፈ ለተፋሰሱ ሀገሮች ሁሉ የተበረከተ የፈጣሪ ስጦታ ነው። ስጦታነቱ አንዱ እጁን አጣምሮ እንዲያየው ሌላው እንዲያለማው ፤ አንዱ የዘፈን ግጥም እየገጠመ ሲቆዝም ለሌላው የማህበረሰባዊ ህይወት ለውጥ መሰረትና የእልልታ ምንጭ እንዲሆን አይደለም።

የወንዙ ውሀ የተፋሰሱን ሀገራት በፍትሀዊነት መጥቀም የሚችል ተፈጥሯዊ አቅም አለው ። ይህንን አቅም ፍትሀዊ በሆነ መንገድ መጠቀም የሚያስችል የውስጥ ፍላጎትና ተነሳሽነት ካለ የወንዙ ውሃ የተፋሰሱን ሀገራት ከፍ ባለ የወንድማማችነት መንፈስ ከማስተሳሰር ባለፈ የተሻለ የጋራ እጣ ፈንታ እንዲጋሩ የሚያስችል ነው።

ኢትዮጺያና ኢትዮጵያውያን ይህንን እውነታ ከፍ ባለ ኃላፊነት ይጋሩታል ። በቀደመው ዘመን የነበሩትም ሆነ አሁንም ያሉት የሀገሪቱ መሪዎች ለዚህ ሀገራዊ እና ታሪካዊ እውነታ የተገዙ ናቸው ። ይህን እንዲያደርጉም መንፈሳዊ፣ ባህላዊና ማህበራዊ እሴቶቻችን ያስገድዷቸዋል።

ኢትዮጵያውያን እንደ ሃገርና ሕዝብ በሌሎች ሕዝቦችና ሀገሮች ጉዳት ላይ የተመሰረተ የጥቅም ፈላጊነት መሻት የላቸውም ፤ ከዚህ ይልቅ አብዛኛው ታሪካቸው ስለነጻነትና ስለፍትህ በተደረጉ ተጋድሎዎች ደማቅ ቀለም ያሸበረቁና በነዚሁ እውነታዎች የተገዙ ናቸው። ከጎረቤት የሚነሳ እሳት የጋራ ጥፋት ምንጭ ይሆናል በሚል ፤ በጎረቤት የተነሳን እሳት ለማጥፋት የሚተጉና ለዚህም የሚያስፈልገውን ሁሉ ዋጋ ለመክፈል የሚያስችል ጠንካራ ስነ ልቦናዊ ውቅር ያላቸው ሕዝቦች ናቸው።

ይህ እውነታ ደግሞ በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሆነ በቅርቡ በሱዳናውያን መካከል ተከስቶ የነበረውን አለመግባባት ለመፍታት የሄዱበት ርቀት ተጨባጭ ማሳያ ነው ። የግድቡ ግንባታና የግንባታው ሄደት ቀደም ባሉት ዘመናት የወንዙን ውሀ አስመልክቶ በግብጽ ህዝብ ላይ የተዘሩ መረጃዎችን የቱን ያህል የተሳሳቱ መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን ህዝቡ በነዚህ መረጃዎች የከፈለው ዋጋ ምን ያልተገባ እንደነበረም ያመላከተ ነው።

ከግድቡ ግንባታ ጀምሮ እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ግንባታው በግብጽ መንድሞቻችን ላይ ሊያስከትል የሚችለው ችግር እንደሌለ በተደጋጋሚ ገልጸዋል። የወንዙ ውሃን በጋራ በማልማት እጣ ፈንታችን ማስተሳሰር የወንዙ ውሃ የያዘው አንዱ በረከት እንደሆነም ለማሳየት ሞክረዋል።

እስካሁን ከተራ የፕሮፓጋንዳ ልፈፋ ባለፈ የግድቡ ግንባታ ሆነ የግንባታው የውሃ ሙሌት በግብጽ ሆነ በሱዳን ወንድሞቻችን ላይ ያስከተለው ችግር የለም ። የግድቡ አንደኛ ሆነ ሁለተኛ ና ሶስተኛ የውሀ ሙሌት ወደታችኛ የተፋሰሱ ሀገራት የሚፈሰውን የውሃ መጠን አልቀነሰውም።ይልቁንም በነዚህ ወቅቶች ሀገራቱ በጎርፍ የመጎዳታቸው እውነታ ውሃው ለሁላችን በቂ ብቻ ሳይሆን ከበቂ በላይ እንደሆነ በተጨባጭ ያሳየ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ወደ ስልጣን በመጡ ማግስት ካይሮ ላይ ተገኝተው ላቅ ባለ የመንድማማችነት መንፈስ “ወላሂ እኛ ግብጽን አንጎዳም “ ያሉበት እውነትም ይህንኑ መሰረት ያደረገ ፤ ከተራ የፖለቲካ ዲስኩርነት ያለፈ፤ በግብጽ ወንድሞቻችን ውስጥ ለዘመናት የተዘራውን አረም በመንቀል አዲስ የመተማመንና የመተባበር የታሪክ ምእራፍ ለመክፈት ያለመ ነበር።

በርግጥም መሪዎቻችን ብቻ ሳይሆን እንደ ሕዝብ እኛ ኢትዮጵያውያን የየትኛውንም ሃገር ሕዝብ የመጉዳት መሻት የለንም ፤ሌሎችን በመጉዳት ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ አስተሳሰብ መሰረትና ይህንን ማድረግ የሚያስችል ማኅበረሰባዊ የአስተሳሰብ ውቅር የለንም። ከዚህ ይልቅ በቀደመው ዘመን ለአፍሪካውያን ወንድሞቻችን የነጻነት ፋናወጊ እንደሆንን ሁሉ በዚህም ዘመን በልማት ፋና ወጊ ሆነን የአፍሪካውያን ወንድሞቻችን ነገዎች ብሩህ ማድረግ ነው ቀዳሚ ዓላማችን።

እንደ ሕዝብ በዚህ ዘመን ይዘነው የተነሳነው ይህ ከፍ ያለ ራዕይ ለግብጽ ሕዝብ የምናጋራው ፤ ለግብጽ ሕዝብ ዛሬ ብቻ ሳይሆን ነገዎችም ከፍያለ ተስፋ የሰነቀና እስከዛሬ ብዙ ዋጋ ያስከፈሉትን ያልተገቡ የስጋትና የጥላቻ ትርክቶችን በመቀየር በአዲስ የትብብር መንፈስ የጋራ እጣ ፈንታችን የምንቀርጽበት ነው።

ባለፈው ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትራችን በአደባባይ በዓለም ህዝብና በፈጣሪ ፊት “ወላሂ እኛ ግብጽን አንጎዳም” እንዳሉት እስካሁን ያለው ተጨባጭ እውነታ ከዚህ የተለየ አይደለም። ሁሉም ነገር በፍትሀዊነት ከዚያም በላይ ከፍ ባለ የኃላፊነት መንፈስ እየተከናወነ ነው።

ይህንን ከሁሉም በላይ እውነታዎችን በሰከነ መንፈስ ለሚከታተለው የግብጽ ሕዝብም ሆነ ለፍትሀዊነትና ለእውነት ለተገዛው የዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ የተሰወረ አይደለም ። እኛ ኢትዮጵውያን መቼም ቢሆን የግብጽንም ሆነ የየትኛውንም ሀገር የመጉዳት ፍላጎት አልነበረንም፤ አሁንም የለንም። ይህንን ሕዝባዊ ቁርጠኝነታችንን ለመግለጽም የጠቅላይ ሚኒስትራችንን ቃል በማደስ “ወላሂ እኛ ግብጽን አንጎዳም “ እንላለን ። ይህ ደግሞ ተራ የፖለቲካ ዲስኩር ሳይሆን የኢትዮጵያውያን በሳል መገለጫና ከማንነታችን የመነጨ ቃል ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## “ወደ ኢትዮጵያ ሰዎች”

ከአስባቸው ደሳለኝ አበሻ (ስንደን)

በድርሰት ስሌት የሰዎችን አመለካከት የተጋነነ ወይም የተዛባ አመለካከት አያደርጉትም ። የሚቀርቡት ፅንሰ ሀሳቦች አንድ ዓይነት ጽንሰ-ሀሳብ ቢመስሉም በውስጣቸው ግን ቅርፅ እና ቀለማቸው ሥዕላዊ መግለጫዎች ሆነው የራሳቸው ትኩረት አግኝተው “የነጥብ ርዕስ” ይሆናሉ። እንዲህ አይነት አፃፃፎች አብዛኛውን ጊዜ የራሳቸው የሆነ ቅንጡ ትርጉም ያላቸው ሰፊ ርዕሶችን የሚዳስሱ የአዕምሮ ስነ-ጥበብ ናቸው።

የስነ-ጥበብ አፈጣጠር ጌጣጌጦች የደራሲውን የአዕምሮ ደረጃ አካላዊ ብቃት ጭምር መግለጫዎችም ናቸው። ስለዚህ የእኔም “የነጥብ ርዕስ” ደራሲ ሔኖክ ስዩም የፈጠራ ስራዎች ውስጥ ከተካተቱ እምቅ ሐሳቦች ውስጥ አንድ ሁለቱን ብቻ ከመፅሀፉ አካል መርጬ መመልከቱ ጠቃሚ ነው ብየ ስለወደድኩ፤ የካቲት ልጆች ለአድዋ ሰዎች የተፃፈችው መልዕት ነፍሴ ገዢታዋለችና የምለውን ልበል።

ከዚያ በፊት ስለደራሲው ትንሽ መስመሮች ማለት እፈልጋለሁ። ይህ የተጎዡ ጋዜጠኛ የሔኖክ ስዩም “ወደ ኢትዮጵያ ሰዎች” የሚለው ትውልድ ጠያቂ ታሪካዊ መፅሀፍ በቃላት እና በቋንቋ አጠቃቀም ላይ ብቻ የተመሠረተ ሳይሆን የአካዳሚክ ርዕሰ-ጉዳይን ባሕልንና ሐገራዊ አብሮነትን ታሪክን የሚዳስስ ዥረት ነው። ደራሲው ሀሳቡን፣ ስሜቱን፣ ልምዱን ወይንም ታሪኩን ባልተለመደ ወይም በባህላዊ መንገድ ለመግለፅ ጎላ አድርጎ የመፅሀፉን ውበት እንዲጠብቅ በማሰብ ልዩ የቋንቋ ችሎታውን ተጠቅሟል።

ወርቃማውን ዘመን የኖሩትን አባቶታችንን የኖሩበትን ጊዜ እና ቦታ መርጦ ዘመንን ተሻግረን በአይነ ሕሊናችን አድዋ ላይ እሳት በሚተፉት መትረየሶች፣ አንገት የሚቀሉ ሰይፍና ጎራዴ ከታጠቁ ጀግኖች ጋር ያጨባብጠናል። ስለዚህ ትውልዱን በማነቃቃትና ወደማይታሰቡ ቦታዎችና ዘመናት ወደኋላ ጨልፎ ከወራት የካቲትን መርጦ ብራናውን ይገልጥልናል። ደራሲው የመረጠው ርዕስ ህይወትን የሚያረጋጋ ሲሆን፤ መጽሐፉ ደግሞ ታአምራትን እየሰራ እንደመጣ ጀግና ትውልድን ይጠይቃል። ደራሲው በምሬትና በቁጭት የሚገልፃቸው እውነተኛ ታሪኮች ሕይወት ያላቸው ቋሚ ምስክሮች ሆነው ነቃሽ እየቆጠረ ሲተርካቸው ቁጭቱ አጥንት ድረስ ዘልቆ ይሰማል።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የእሳተ ገሞራ ፍንዳታዎች ያህል የሚያስደነግጡ የትውልድ ስህተቶችን ነቅሶ በብዕር ይፋለማቸዋል። በብዕር ፍትህ ይጠይቅባቸዋል። በብዕር ዳኝነት ይሰጥባቸዋል። ደራሲው ሔኖክ ስዩም በመሬት ስበት እና በውቅያኖስ ማዕበል ላይ ለውጥ ያስከተለ እስከሚመስል ድረስ ትውልዱ በሀይለኛ የዘረኝነት ሱናሚ እየተመታ ባለበት በዚህ ክፉ ጊዜ የምፅዓት ቀን ከመምጣቱ በፊት መከላከያ የሚሆናቸውን ኢትዮጵያኒዝም ጃኖ እንዲያጠልቁ ይህንን “ወደ ኢትዮጵያ ሰዎች” የተሰኘ መፅሀፍን አበርክቶልናል።

ደራሲው መፅሀፉን የጀግኖችን ሥነ-ልቦና፣ የፍቅር የጓደኝነት እና አገራዊ የተስፋ ታሪክን እንዲያሳይ አድርጎ ከትቦታል። ተገገዡ ጋዜጠኛ ሔኖክ ስዩም በድርሰት ችሎታው በሐገራችን ቀደም ሲል ከነበሩት በጣም ምርጥ ታዋቂ ጸሐፊዎች መካከል እንደነ በአሉ ግርማ፤ እንደ ብርሀኑ ዘሪሁን፣ እንደ ተክለ ፃድቅ መኩሪያ፣ እንደ ሀዲስ አለማየሁ፣ እንደ ጳውሎስ ኞኞ፣ እንደ ፀጋዬ ገብረመድህን፣ እንደ ስብሀት ገ/እግዚአብሔር፣ እንደ ማሞ ውድነህ የመሳሰሉ አሻራቸውን ትተው ካለፉት፤ አሁንም በህይወት ካሉት እንደ አለማየሁ ገላጋይ፣ አዳም ረታ፣ እንዳለ ጌታ ከበደ፣ ወዘተ ከመሳሰሉ ዝነኛ የኢትዮጵያ ክላሲክ የሆኑ ፀሀፊዎች እግር ከእግር እየተከተለ የሚጓዝ ብቃት ያለው ወጣት ደራሲ ሲሆን፤ አንድ ቀን ከነዚህ ታላላቅ ደራሲዎች ተርታ ስሙን በወርቅ ቀለም እንደሚያፅፍ እርግጠኛ ነኝ።

ቀደም ባሉት ጊዜያት የተጓዡ ጋዜጠኛ ሔኖክ. ስዩምን ሁለቱን፣ መፃህፍቶችን አንብቢያለሁ። ይህኛው ሶስተኛየ መሆኑ ነው። የደራሲው ብዕር የሰውን ነፍስ ሥነ-ልቦና በዘዴ የሚያሳዩ እፁብ ድንቅ ሥራዎች በመሆናቸው የተዋጣላቸው የመንፈስ ምግቦች ናቸው። በተለይ ሶስተኛው የተጓዡ ጋዜጠኛ መፅሀፍ “ወደ ኢትዮጵያ ሠዎች” በአርበኝነት ጦርነት ወቅት ስለ ኢትዮጵያ ክቡር ሕይወታቸውን ሲገብሩ የኖሩትን የአድዋ ትውልዶች ይዘክራል።

“ሰው ወድቆ ሐገር ቆሟል። በዚያ ጀግና አፈር በልቶ የሐገር ክብር አፈርን አራግፎ ህያው ሆኖል”። የወደቁት በወደቁበት አልቀሩም። ስማችንና ዘመናችንን ይዘው ተነሱ። ሞት ለጀግኖች ሲሆን ትንሳኤው ግን ለኛ ሆነ፤” በማለት መፅሀፉ መጠነ ሰፊ ሥራውን በብዙ የታሪክ መስመሮችን አካቶ ይዟል።

በመፃፉ ውስጥ የሚያነሳቸው የአድዋ ጀግኖች ታሪካቸው ነፍስ ዘርቶ ህያው ገድል ሲሰሩ ጥቁሩን የሱናሜ ንጉስ እምዬ ምኒልክ እና ብርሀን ዘኢትዮጵያ እቴጌ ጣይቱ ብጡልን ጠቅሶ የውጊያ ትዕይንቶቻቸውን በምናብ ያሳየናል። የዛሬዋ ኢትዮጵያ እንዴት እንደቆሞች የሙታን አፅም(በጀግንነት የወደቁትን) አነጋግሮ አፈር የማያበላሸውን ታሪካቸውን አገላብጦ ትውልድን እየጠየቀ ታሪኩን ይዘክራል።

በዚህም “ሰው ተከፍሎ ለሰው ሀገር በማኖሩ አህጉር ያስመካ ድል እውን ሆኖ በዚያ ድል አንዲት ሐገር ብቻ ሳትሆን ፍትህ የሚጋሯት ሁሉ ቀና ብለዋል።” ይልና፤ በታላቅ ንጉስ መሪነት የጥቁር ድል በጥቁር ሕዝቦች ተፃፈ፤ የካቲትም ብራናው ሆነች፤ ኢትዮጵያዊነትም ቀለም ሆነ፤” በማለት ህያው ምስክርነት ይሰጣል። በተለይ “ጥቃት”ን ሐገራዊ ፋይዳ በመስጠት ሂደት ውስጥ በሰዎች እና በአካባቢ ላይ ሊደርስ የሚችልን ጉዳት እንዳይደርስ መከላከል ስለመሆኑ በማንሳት፤ የዘር ፖለቲካ እንደምስጥ አንክቶ በበላው ቂላ ቂል ከንቱ ትውልድ ውስጥ ደራሲው ቁጭቱን እንኳን የሚገልፅበት አቅም ሲያጣ ይስተዋላል።

“ከአድዋ ጀግኖች አልተማርንም። ለየ ብቻችን ቆመን ግን ተሸነፍን!። ለየብቻ ቆመን የታገልንባቸው አውደ ውጊያዎች ኪሳራ እንጅ ክብር አልነበራቸውም። አድዋ ግን እንደ ዜጋ አልተገለለም። ንጉሰነገስቱ ሁሉን ጠሩ። ሁሉም ባለቤት ነበረ። ሁሉም ባለቤት ሲሆን ድል አለ። አድዋ የባለቤትነት ውጤት ነው፤” ይለናል። በአሁኑ ኑባሬያችን እየተቆጨም፤ አሁን ግን ተባብረን ማድረግ የምንችለውን ሳናደርግ እንደ ሐገር ተያይዘን ወድቀን ተያይዘን መነሳት አቅቶን እርስበእርስ ስንገዳደል የአይን ምስክር ሆኖ ለትውልዱ አቤት ይላል።

የአድዋ ልጆች የአለም መሳቂያ ለማኞች ሆነናል። በቁጭት ስሜት ብቻ ተስፋ ቆርጠን ከዛሬ ይልቅ ነገም የተሻለ ቀን እንዳለ ማሰብ ስለአቃተን በዘርና በቋንቋ ኮሮጆ ውስጥ ተደብቀን መሰማማት አቃተን። ከወደቅንበት እጅ ለእጅ ተያይዞ መነሳትና አንድ ሆነን መቆም አቃተን። ... እያለ በመዘርዘር ደራሲው በአድዋ መንፈስ ይቀናል። ይሄንንም ሲያብራራ “እኔ አድዋን ባሰብኩ ጊዜ ነፍስም አይቀርልኝ። “ስለምን” ብትሉ፤ እቀናለሁ። በመንፈሳችንም እቀናለሁ። ልትቀኑ የሚገባው ለሐገር በተከፈለ ተግባር ነው። የአድዋ መንፈስ ያስቀናል። አድዋ ለዘላለም ተቆፍሮ የሚወጣ ነዳጃችን ነው። ዘላለም ተነግሮ የማይጠገብ፤... እያለ ይቀጥላል።

በየካቲት እውን የሆነችው ድል የአንድ ግንባር ጦርነት ፍፃሜ ብቻ ሳትሆን ዘመን ድንበር የማያበጅላት የነፃነት ዘለአለም ናት። ምክንያቱም በዚያ ዘመን እውነት ሀሰትን አሸንፋለች፤ በዚያ ሰው ወድቆ ሐገር ቆሟል፤ በዚያ ጀግና አፈር በልቶ የሐገር ክብር አፈሩን አራግፎ ህያው ሆኗል። እናም ደራሲው ይህንን ሁሉ ቁጭቱን ሲናገር እንዲህ ይላል፡- እናንተ የሐገሬ ሰዎች... ይህንን ድምፅ እንደ አንድ የራሴን ልጩህ ብሎ እንደወጣ ድምፅ ቁጠሩት፤ በምድረበዳ ሳይሆን በመካከላችሁ እንዳለ ድምፅ ጆሮ ስጡት፤” በማለት ለትውልዱ እየቃተተ መፅሀፉ ላይ በፊደል ታግዞ ምሬቱን ያስተጋባል።

እኔም እላችኋለሁ እናንተ የሐገሬ ልጆች ምናልባት ይህንን መፅሀፍ ስታነቡ የደራሲውን ጩኸት በትክክል ልትረዱት ትችላላችሁ፤ ለእኔ አይነቱ በሰው ሐገር በሰው ታሪክ መንፈሱ ለሚረበሽ ትውልድ ግን ደራሲው ከሕይወት እድሜው ቆንጥሮ እንደለገሰን አድርጌ እቆጥረዋለሁ።

ከዚህም ባለፈ፣ ሔኖክ ስዩም “ወደ ኢትዮጵያ ሰዎች” በሚለው መፅሐፉ አዲሱንም ሆነ ቀጣዩ ትውልድ በማይነጥፍ ጥበብ እንደገና ምርኩዝ ሆኖ መርቷልና ኮምፓስ ሆኖ አቅጣጫ አሳይቶናልና ምስጋናዬ ባለህበት ይድረስልኝ። ለዛሬው በዚሁ አበቃሁ በሌላ ዝግጅት እስከንገናኝ ቸር ይግጠመን።

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# የሟርት ፓለቲካ

ባለቅኔውና ወግ ሰላቂው በእውቀቱ ስዩም በፊስ ቡክ ሰሌዳው ላይ ሰሞነኛውን ሟርት በጨዋ ደንብ እውቅና የሰጠ ሌላ ገደምዳሜ ሟርትን ፤ "ታሪክን ወደ ኋላና ወደፊት"በሚል ርዕሰ አስነብቦናል። ለነገሩ ለበእውቀቱ ሟርት ብርቁ አይደለም። ከዚህ ቀደም "ሟርት"የሚል ሟርትም በ"በራሪ ቅጠሎች"አሟርቶልን ያውቃል። ሟርት ይፈራል። ይጠላል ። ደግሞ እንዲህ ያሟርታል ፡-

"ያልተበረዘውን የኢትዮጵያ ታሪክ የሚያነብ ሰው ፥ መጀመሪያ የሚመጣለት ስሜት " ምን ጉድ ነው ?" የሚል ነው ፤ ለምሳሌ ነገስታት አንድ ልማድ ነበራቸው፤ ልክ ዙፋን ላይ ሲወጡ ልጆቻቸውን እና ወንድሞቻቸውን ሰብስበው ከመዲናቸው ራቅ ያለ ማጎርያ ቦታ ያስቀምጧቸዋል ፤ የማጎርያው መልክአምድር ለማምለጥ አይመችም ፤ ከዚያም አልፎም ፤ በንቁና አስፈሪ ዘበኞች ይጠበቃል፤ በአክሱም ዘመን ደብረዳሞ የልኡላን ማጎርያ ሆኖ አገልግሏል ፤ የሸዋ ነገስታት በተራቸው ሲገዙ ፤ ለዚህ ተግባር የመረጡት ቦታ ፥ ወሎ ዛሬ ግሼን ማርያም የምትገኝበትን አምባ ነበር ፤ የጎንደር ነገስታት በበኩላቸው ዘመዶቻቸውን "ወህኒ" ወደ ተባለ ስፍራ ማጋዝ ጀመሩ፤ ወህኒቤት የሚለውን ቃል የወረስነው ከዚህ ስፍራ ነው ፤ ወህኒ በመሰረቱ የፖለቲካ እስር ቤት ሲሆን ፥ የመጀመርያው የፖለቲካ ወንጀል ከንጉስ መወለድ ነበር፤

ንጉሱ ድንገት ወራሹን ሳያሳውቅ በጦር ሜዳ ይገደላል እንበል፥ አንዱ የቤተመንግስት መኮንን ብድግ ይልና አንዱን ልኡል ከማጎርያ ቤት አውርዶ ዙፋን ላይ ያወጣዋል፤ ሌላው የጦር አዝማች ደግሞ የኔን ምርጫ ካላነገስኩ ሞቼ እገኛለሁ ብሎ ይነሳል፤ ባንጋሾች መካከል የሚደረገው ፉክክር መዲናይቱን ባንዴ ወደ ፍርስራሽ እና ያስከሬን ክምር ይቀይራታል።

የቀድሞ ሰዎች እንዲህ አይነቱን ብሄራዊ አደጋ ለመቀነስ የፈጠሩት "ዘዴ " የንጉስን ሞት መሰወር ነበር ፤ የንጉስ ሞት ቀርቶ ህመሙ እንኳ ለህዝብ ይፋ አይደረግም፤ በዘመነ መሳፍንት ጊዜ ፥ የየጁው ራስ አሊ ሲሞት ፤ አንድ አሳባቂ ( የዘመኑ ፓፓራዚ) ወሬውን አሾለከው፤ ወድያው የረጋው አገር መላወስ ጀመረ፤ ጉዳዩ ያሳሰባት አንዲት አልቃሽ እንዲህ ብላ ገጠመች፥

" እሻ እሻ ነው እንጂ የእስራኤልን ሞት
እንዲያልቅሰው አሊን ለምን ቀበሩት "

" እሻ እሻ " ማለት ዝም በሉ ጸጥ በሉ ማለት ነው፤ በዘመኑ የንጉስ ወገን ነን የሚሉ ሰዎች ዘራቸውን ከሰለሞን ስለሚመዝዙ " እስራኤል " በሚል የወል ስም ይታወቃሉ፤

በግጥሙ መስመር ላይ ያለው ህብረቃል " እንዲያልቅሰው " የሚል ነው፤ ሰሙ " እንዲህ አልቅሰው " ሲሆን ወርቁ " ሰው እንዲተላለቅ" የሚል ትርጉም አለው ፤ ባጭሩ አልቃሺቱ፥

" ህዝብ እንዳይተላለቅ የንጉስ ሞት ይደበቅ " ማለት ነው የፈለገችው ፤ ከጥንት እስከዛሬ አገረ መንግስታችን የሚቆመው ባንድ ሰው ትከሻ ላይ ነው ፤ መሪ ሲታመም አገር ይታመማል፤ መሪ ሲሞት አገር በጥቂቱ ይሞታል፤ ይህንን መለወጥ የሚቻለው እንዴት ነው? የማይሞቱ ተቋሞችን በመገንባት ፤ የማይታመሙ ህጎችን በመመስረት? ወይስ ሌላ መላ አለ? "በማለት ይቋጫል ።

የበእውቄ ይቺ ሾካካ ታሪክ ቀመስ ሟርት ላለፉት አንድና ሁለት ሳምንት በማህበራዊና በመደበኛ ሚዲያው በስፋት ሲነዛ የሰነበተ ሟርት ቅርሻ ናት። ሆኖሞ የዘመነ ኋሊነትና የእውነታ/fact/ጥያቄ ሊነሳባት ይችላል። አይደለም የ18ኛውንና የ19ኛውን መክዘ ዘመነ መሳፍንት ከዛሬው መግስት ጋር ማነጻጸር፤ የመለስን አገዛዝ ከዐቢይ አስተዳደር ለማነጻጸር መሞከር እንኳ ጥያቄ ያስነሳል ። ሁለቱም በዘመናቸው ከነበሩ አቻ ገዢዎችና መሪዎች ጋር ቢነጻጸሩ ይበልጥ አግባብነት ይኖረዋል ።

የእጅ ስልክ ያለው ሕዝበ አዳም ሁሉ መረጃ ነጋሪ በሆነበት ፤ የእጅ ስልክና በይነ መረብ ጓዳ ጉድጓዱን ባዳረሰበት 21ኛው መክዘ አይደለም የሀገር መሪ ህመምና ሞት የእኔ ቢጠው በጉንፉን ቢያዝ ከብርሃን ፈጥኖ ለቢጤው ይደርሰዋል። እውነት እንነጋገር ከተባለ በሀገሪቱ ዘመናዊ ታሪክ ለዛውም ቀውስ እንደ ጫጩት በሚቀፈቀፍበት ሀገር እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ለተቋማት ግንባታ ትኩረት የሰጠ መሪ የለም ። የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድን፤ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽንና ሌሎችን በአብነት ማንሳት ይቻላል። የማንኩሳውን በእውቄ ሟርት ለመንደርደሪያነት ያህል ካነሳሁ ስለሚበቃ ወደ ዋናው ሟርት ልመለስ ።

ይህን ስል ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ ፍጹም ናቸው፤ በፕሬዚዳንትነት የሚመሩትና የመሠረቱት ብልጽግና ሙሉኡ በኩልሄ ነው እያልሁ አይደለም። የማይታረቁ ቅራኔዎች ፣ እልፍ አእላፍ ፍላጎቶችና መሳሳቦች ፣ ለግማሽ ክፍለ ዘመን ልዩነት ተቋማዊና መዋቅራዊ ሆኖ በተነዛበትና የጋራ አካፋይ በሌለበት ሀገር ይቅርና በአንጻራዊነት አልጋ በአልጋ በሆነበት ሀገርም ስህተትና ቀውስ ይፈጠራል ። እንኳን ትላንት የተመሠረተው ብልጽግና ዲሞክራት ይሁን ሪፐብሊካን፣ ሌበር ይሁን ቶሪ ፣ 100 አመትን የተሻገረው የደቡብ አፍሪካው ኤኤንሲ ፣ አልያም ወደ 70 አመት የተጠጋው የጃፓኑ ኤልዲፒ ይሁን የቻይናው ፓርቲ ከስህተትና ከቀውስ አምልጠው አያውቁም ። ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ ብልጽግናንም ሆነ ፕሬዚዳንቱን ወይም ጠቅላይ ሚንስትሩ በሀሳብ መሞገትና መተቸት ከፍ ሲልም አማራጭ የፓሊሲ ሀሳብ አቅርቦ መቃወም እየተቻለ ሟርትን ምን አመጣው ።

በእኛ፣ በቤተሰባችን፣ በጓደኞችን በዘመድ አዝማዳችን እንዲደርስ የማንፈልገውን ሞት በእሳቸው እንዲደርስ እንዴት እናሟርታለን ፤ ታላቁ መጽሐፍስ፡-" እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው ፤ ሕግም ነቢያትም ይህ ነውና።" ( የማቴ ወን 7 ፥ 12) አይደል የሚለው ፤ ሶስቱ አብርሀማዊ ዕምነቶችን ካስተሳሰሩ ትዕምርቶች አንዱ ፤

" በራስህ ላይ እንዲደረግ የማትፈልገውን፤ በሌሎች ላይ አታድርግ ፤"አይደለምን የሚለው !?

ቁጥራቸው ቀላል ያልሆኑ የግል መደበኛ ሚዲያዎችና ብዙ ተከታይ ያላቸው አንቂ ተብየዎችና ዩቲውበሮች ፤ የተቃዋሚ ፓለቲካ አመራሮች ሳይቀሩ ነጋ ጠባ ሲሰልቁትና ሲያነሱ ሲጥሉት የሰነበተው ሟርታ የጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አሕመድን መጥፋት ነው። በተለያዩ አጋጣሚዎችና ሁነቶች ቶሎ ቶሎ በሚዲያ ሲታዩ የማይንበለበል የትችት ፍላጻ የለም። እንደ እዚያ ሰሞን ከካሜራ እይታ ዘወር ሲሉ ደግሞ አንድ ጊዜ ታመው ነው ፣ ሌላ ጊዜ ሞተው ነው በሚል ሟርት አየሩንና መልካውን ይቆጣጠሩታል ።

**የሀገራችን የፓርቲ ፓለቲካ ገና ጨቅላ ነው። ያልበሰለ ጨርቃ ነው ። በእድሜም በአስተሳሰብም ለጋ ነው ። ብዙ ይቀረዋል። በ1960ዎቹ በተማሪ ንቅናቄ የተሟሸና የተጋገረ ነው። ገና ከ70 አመት ያልዘለለ ሩጦና ዘሎ ያልጠገበ ጉብል ህጻን ነው**

የዚህን ሟርት መነሻም ሆነ የሟርተኞችን ግብ ከተለያየ ማዕዘን መተንተንና መበየን ቢቻልም የሟርቱ ዋና ዛቢያና ማጠንጠኛ ግን ራሱን በጠላትነትነት ያሰለፈ ኃይል ጠላቴ ብሎ ለፈረጃቸው ጠቅላይ ሚንስትር ያለውን ክፉ ምኞት የገለጸበት ነው ። በዚህ ቀውጢ ሰዓት በእሳቸው ላይ የሚሟረት ሟርት በኢትዮጵያና በመላው ኢትዮጵያዊ ላይ የተሟረተ መሆኑን ይሄ ክፉ ኃይል አልተረዳም ። ቢረዳም ለሀገርና ለዜጋ ግድ እንደሌለው አረጋግጦልናል ።

ላለፉት አራት አመታት ከታሪካዊ ጠላቶቻችን ጋር ግንባር ገጥሞ በሀሰተኛ መረጃ ፣ ሕዝብ እንዲነሳባቸው ሌት ተቀን በመቀስቀስ ፣ በብልጽግና መካከል መከፋፈል በመፍጠር ፣ መከላከያን በብሔርና በሀይማኖት በመለያየት ፣ ኢኮኖሚውን በማሻጠር ፣ የእርስ በርስ ጦርነት በመቀስቀስ ፣ በውክልና ጦርነት፣ ነፍጥ በማንሳት ፣ በግድያ ሙከራ፣ ወዘተረፈ ሊያጠፉቸው ያልፈነቀለው ድንጋይ ባይኖርም ሊሳካለት ስላልቻለ ወደ ሟርተኛነት ወርዷል ። ወደ የሟርትና የጥንቆላ ፓለቲካ ዘቅጧል ።

ይህ የሟርተኛና የጠንቋይ ስብስብ ያልተረዳው ሀቅ በዚህ ቀውጢ ሰዓት ለዛውም ተቋማት ገና ዳዴ ዳዴ እያሉ ባለበት ሁኔታ የአመራር ክፍተት ተፈጠረ ማለት ሀገርን ወደለየለት ቀውስ የማንደርደር ሲከፋም ሀገርን ለውጭ ወረራና ለእርስ በርስ ጦርነት የመዳረግ እምቅ አደጋ መኖሩ ነው። በተዘዋዋሪ እነዚህ ሟርተኞችና ጠንቋዮች ኢትዮጵያ እንድትታመምና እንድትሞት ነው እያሟረቱ ያሉት። አሁን ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታ መሪ ቢሄድ መሪ ይመጣል የሚያስብል ዋስትናም ነባራዊ ሁኔታም የለም ። ሌላው ይቅርና በገዥው ፓርቲ ብልጽግና ያለውን መሳሳብና መወነጃጀል የምናውቀው ነው። የፓርቲው ውስጠ አካላቱ እንደ ሌሎች ተቋማት ገና አልጸናም። ተሰርቶ አላለቀም። የፓርቲ ፓለቲካችን የተቋማት ግንባታው አካል መሆኑም ሊዘነጋ አይገባም ።

የሀገራችን የፓርቲ ፓለቲካ ገና ጨቅላ ነው። ያልበሰለ ጮርቃ ነው ። በእድሜም በአስተሳሰብም ለጋ ነው ። ብዙ ይቀረዋል። በ1960ዎቹ በተማሪ ንቅናቄ የተሟሸና የተጋገረ ነው። ገና ከ70 አመት ያልዘለለ ሩጦና ዘሎ ያልጠገበ ጉብል ህጻን ነው። ለሀገርና ለፓርቲ ሲሆን 70 አመት 7 አመት ነው የሚል ዕምነት አለኝ። የአልበርት አነስታይንን የአንጻራዊነት ቀመር እዚህ ላይ ያስታውሷል ። የሀገረ መንግስትና የፓለቲካ ታሪክ የሰው ልጅ እድሜ እንደሚሰላው አይሰላም። ከፍ ብሎ ለመግለጽ እንደተሞከረው የሀገራችን ዘመናዊ የፓለቲካ ታሪክ መነሻው የተማሪዎች ዕንቅስቃሴ ነው።

በተማሪዎች የ1960ዎች ዕንቅስቃሴና በፓለቲከኛነት ስማቸው ቀድሞ የሚነሳው እነ ኃይሌ ፊዳ ፣ ተስፋዬ ደበሳይ፣ ብርሀነመስቀል ረዳ፣ ግርማቸው ለማ ፣ መለስ ተክሌ ( የቀድሞው ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ ስሙን የወረሱት)፣ ሰለሞን ዋዳ ፣ ጥላሁን ግዛውና ዋለልኝ መኮነን ለፓርቲ ፓለቲካ መሠረት ከጣሉት ይገኙበታል። ኢህአፓም ሆነ መኢሶን ወይም በዘመኑ እንደ አሸን ፈልተው የነበሩ የፓለቲካ ፓርቲዎች መሠረት የሀገር ቤትና የውጭም ተማሪዎች ንቅናቄዎች ናቸው ። የሁሉም ፓርቲዎች ርዕዮተ አለም ከሞላ ጎደል ሶሻሊዝም መሆኑና ከሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የማይጣጣምና እንዳለ ከውጭ የተገለበጠ መሆኑ ዛሬ ለምንገኝበት ምስቅልቅል ዳርጎናል። መውጫ አሳጥቶናል ። ፓለቲካችንን ወደ ሟርት ፣ ጥንቆላ፣ አስማት፣ ምቀኝነት ፣ ቅናት ፣ መጠላለፍ ፣ መበላላት ፣ አሉባልታ ፣ ውሸት ፣ ወዘተረፈ አውርዶታል።

በፈጠራ ትርክትና በግልብ ትንተና መታገያና ማታገያ ሆኖ የመጣው የብሔር ጥያቄ ሀገራችን ዛሬ ድረስ ለምትገኝበት ምስቅልቅል እና አጣብቂኝ መግፍኤ ከመሆኑ ባሻጋር ፤ ሀገር ፣ ሕዝብና የባህር በር አሳጥቶናል። ከዚያን ጊዜ አንስቶ ልሒቃኑን በሁለት ጎራ ከፍሎ እያባላና እያጨቃጨቀ ይገኛል። በሀገራችን ተንሰራፍቶ የነበረው ጭቆና የመደብ ነው አይደለም የብሔር ጭቆና ነው በሚሉ ሁለት የማይታረቁ ቅራኔዎች ተጠምዷል። የብሔር ጭቆና በተጠየቃዊነት በምክንያታዊነት የሚተነተን ሳይሆን በማንነት በስሜት የሚቀነቀን የሚራገብ መሆኑ ልዩነቱን የማጥበብ ሂደቱን አዳጋች አድርጎታል ።

እዚህ ላይ በህወሓት ፣ በኦነግ እና ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነትን በሚያራምዱ ወገኖች መካከል ያለውን ልዩነት በአብነት ማንሳት ይቻላል ። ሆኖም የተማሪዎች እንቅስቃሴ ለትህነግ ፣ ለኦነግና ለሌሎች የብሔር ድርጅቶች መፈጠር እርሾ ሆኖ ማገልገሉ አይካድም ። የጋራ ሀገር ፣ ታሪክና ጀግና እንዳይኖረን አድርጓል ። ጥላቻ ፣ ልዩነትና ጎሰኝነት እንዲጎነቁል ለም አፈር ሁኗል ። የሀብት ብሔርተኝነትን ተክሏል። ጦዞ ጦዞ ፣ ጉኖ ጉኖ ፣ አርጦ አርጦ መጨረሻው ሟርትና ጥንቆላ መሆኑ ሳያንስ ምትክና ቅያሬ የሌላትን ሀገር ለማፍረስ ጎዝጉዞ እያሟረተ ይገኛል ። ቁርጡን ይወቅ ፤ በሟርት ሀገር አይፈርስም ። ስልጣን አይገኝም። ሀገራችን ኢትዮጵያ ከሟርት በላይ ናት ።

ሀገራችን ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጇቿ ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኖራለች !

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ዓለም አቀፋዊ የቴክኖሎጂ ትስስርን ለዘላቂ የምጣኔ ሀብት እድገት

አንተነህ ቸሬ

ቴክኖሎጂ እያንዳንዱን የዓለም እንቅስቃሴ እየተቆጣጠረ ባለበት በአሁኑ ወቅት፣ ዘላቂ የምጣኔ ሀብት እድገትን ከቴክኖሎጂው ዘርፍ እድገት ውጭ ማሰብ የሚቻል አይሆንም። ዛሬ በምጣኔ ሀብታቸው የዓለማችን ቁንጮ የሆኑት ልዕለ ኃያላን ሀገራት የቴክኖሎጂ ዘርፋቸው እጅግ የተራቀቀ ነው። እነዚህ ሀገራት አሁን ያሉበት የቴክኖሎጂ ደረጃ ላይ የደረሱት ዘርፉ በየጊዜው እድገትንና መሻሻሎችን እንዲስመዘግብ ባከናወኗቸው ተግባራት ነው።

ጀማሪ ለነበሩት የቴክኖሎጂ ተቋሞቻቸው ያደረጓቸው ልዩ ልዩ የሕግና የፋይናንስ ድጋፎችና ማበረታቻዎች ተቋማቱ አሁን ያሉበት ደረጃ እንዲደርሱ አግዟቸዋል። ሀገራቱ በቴክኖሎጂ ተቋሞቻቸው መካከል የልምድ ልውውጥ እንዲኖርና የገበያ ትስስር እንዲፈጠር በማድረግ ጀማሪዎቹ ከትልልቆቹ እንዲማሩና አቅማቸውን አጎልብተው በሀገራቱ እድገት ላይ ትልቅ አሻራ እንዲኖራቸውና በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ አድርገዋል።

ትልልቅ የቴክኖሎጂ ኤክስፖዎች በቴክኖሎጂ ተቋማት መካከል ያለውን ግንኙነት በማዳበር ለጀማሪ የቴክኖሎጂ ባለሙያዎች የልምድ ልውውጥና የገበያ ትስስር አቅም ማደግ ትልቅ አስተዋፅኦ አላቸው። መሰል የቴክኖሎጂ ኹነቶች የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ከማስተዋወቅ ጀምሮ የዘርፉን ተዋንያን በገበያና በፈጠራ በማስተሳሰር የተሻሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እውን እንዲሆኑም ያግዛሉ።

ይህንኑ ዓላማ ያነገበው የአፍሪካ የቴክኖሎጂ ኤክስፖ (African Tech Expo 2022)፣ ከጳጉሜ ሁለት ቀን 2014 ዓ.ም አንስቶ ለሶስት ተከታታይ ቀናት በአዲስ አበባ ስካይትላይት ሆቴል ይካሄዳል። ኤክስፖው በኢትዮጵያ ሲካሄድ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሆን፤ ከመላው ዓለም የሚመጡ ከ250 በላይ የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ የቴክኖሎጂ ተቋማት እንደሚሳተፉበት ተገልጿል።

የዘንድሮው የአፍሪካ የቴክኖሎጂ ኤክስፖ በጆርካ ኤቨንትስ (Jorka Event Organizers PLC) እና በኤ.ቲ.ኤክስ (ATX) ትብብር የሚዘጋጅ ሲሆን በአፍሪካ፣ በእስያ፣ በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ የዘርፉ ተዋንያን ይሳተፉበታል። የቴክኖሎጂ ባለሙያዎችንና ፖሊሲ አውጭዎችን ጨምሮ ሌሎች የዘርፉ ባለድርሻ አካላት በሚሳተፉበት በዚህ ኤክስፖ ላይ፤ የታዳሽ ኃይል ቴክኖሎጂ፣ የዲጂታል የክፍያ ስርዓት፣ የቴሌኮሙኒኬሽን እና የፋይናንስ ቴክኖሎጂዎች ዐቢይ ትኩረት የሚደረግባቸው ዘርፎች ይሆናሉ።

በኤክስፖው የሚሳተፉ አካላት የተሰማሩባቸው የምርትና አገልግሎት ዘርፎች በርካታ ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹም ፡-

* የሮቦቲክስ
* የብሎክቼይን
* የሳይበር ደህንነት
* የባዮቴክኖሎጂ
* የደህንነትና ስለላ
* የባንክ
* የፀሐይ ኃይል
* የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች
* የማኅበራዊ ሚዲያ
* የኮምፒዩተር እቃዎች
* የቤት ውስጥ መገልገያዎች
* ሞባይልና ኤሌክትሮኒክስ
* የኢንተርኔት
* የመድኃኒት
* የግብርና ማሽኖች
* የግንባታ እቃዎች
* የተሽከርካሪዎች
* የፕላስቲክ




* የሆቴል እቃዎች
* የኢንዱስትሪ ቁሳቁስ ... ቴክኖሎጂዎች ናቸው።

የአፍሪካ ቴክኖሎጂ ኤክስፖ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚገኙ ትልልቅ ኩባንያዎችም ይሳተፉበታል። ከእነዚህ ትልልቅ ኩባንያዎች መካከል ‹‹ማይክሮሶፍት›› (Microsoft)፣ ‹‹ሜታ›› (Meta)፣ ‹‹አማዞን››፣ (Amazon)፣ ‹‹ጁሚያ›› (Jumia)፣ ‹‹ኦራክል›› (Oracle)፣ ‹‹ቻይና ዩኒኮም›› (China Unicom)፣ ‹‹አክሰስ›› (Access) እና ሌሎችም ስመ ጥር ግዙፍ የቴክኖሎጂ ተቋማት ይጠቀሳሉ።

የእነዚህ ተቋማት ተሳትፎ በራሱ ብዙ ፋይዳዎች አሉት። ተቋማቱ በዘርፉ የካበተ ልምድ ያላቸው በመሆኑ ተሳትፏቸው ሌሎች አካላት፣ በተለይም ጀማሪ የቴክኖሎጂ ተቋማት፣ ልምድ እንዲቀስሙ የማድረግ እድል ይፈጥራል። የሥራ ትስስር በመፍጠርም ጀማሪዎቹ ከትልልቆቹ ልዩ ልዩ ድጋፎችን እንዲያገኙ ያስችላቸዋል።

የቴክኖሎጂ ኤክስፖው አዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለማስተዋወቅም እድል ይፈጥራል። ይህም የኤክስፖው ተሳታፊዎች በሚያተኩሩባቸው ዘርፎች (ኤሌክትሮኒክስ፣ ሮቦቲክስ፣ ፋይናንስ፣ ኢንተርኔት፣ ኮምፒዩተር ...) ያሉና ዘመኑ የደረሰባቸውን የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለማወቅና በቴክኖሎጂዎቹ ላይ ተመስርቶ ስራን ለማቀድ ያግዛል።

ኤክስፖው ለቴክኖሎጂ ተቋማቱ፣ ለተጠቃሚው፣ ለፖሊሲ አውጪዎች እና ለሌሎች የዘርፉ ባለድርሻ አካላት ብዙ ጥቅሞችን እንደሚያስገኝ ይጠበቃል። የቴክኖሎጂ ተቋማት ምርቶቻቸውና አገልግሎታቸውን ለማስተዋወቅ እንዲሁም ከሌሎች አጋሮቻቸው ጋር የሥራ ትስስርና የልምድ ልውውጥ ለመፍጠርም ያግዛቸዋል። ተጠቃሚዎች በበኩላቸው የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለማወቅና የምርቶቹ ተጠቃሚ ለመሆን ያስችላቸዋል፤ከዚህ በተጨማሪም ከተቋማቱ ጋር ግንኙነት ለመመስረት ይረዳቸዋል። ፖሊሲ አውጪዎች ደግሞ የዘርፉን አጠቃላይ ቁመና ለመገንዘብ፣ ክፍተቶችን ለመለየትና ዘርፉን በብቃት ለመምራት የሚያስችሉ ሕጎችን ለመቅረፅ ግብዓቶችን ለመሰብሰብ ይጠቀሙበታል።

የጆርካ ኤቨንትስ ማርኬቲንግና ኮሙኒኬሽንስ ኃላፊ አቶ ሳምሶን ኃይለኢየሱስ ኤክስፖው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ተናግረዋል። እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ከኤክስፖው ዓላማዎች መካከል አንዱ የአፍሪካን የቴክኖሎጂ ገበያ ለኢትዮጵያውያን ባለሀብቶችና አምራቾች ማስተዋወቅና መክፈት ነው። ኤክስፖው የሚፈጥረው የስራ ግንኙነትና ትውውቅ የገበያ ትስስር እንዲጎለብት ያደርጋል። ይህ የገበያ ትስስር ደግሞ ለአገራዊ ምጣኔ ሀብት እድገትና ለዘርፉ ማደግ አስተዋፅኦ ያበረክታል።

የኢትዮጵያን መልካም ገጽታ ለመገንባትም ጥሩ አጋጣሚ ይፈጥራል። ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚመጡ ትልልቅ ዓለም አቀፍ የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች በኤክስፖው ስለሚሳተፉ የኢትዮጵያን በጎ ገጽታ ለማሳየት እድል ይፈጥራል። ይህም ኀብኚዎችም ሆኑ ኢንቨስተሮች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ በማበረታታት ዘርፈ ብዙ ሀገራዊ ጥቅሞችን ያስገኛል።

ኢትዮጵያ የንግድና ኢንቨስትመንት መዳረሻ እንድትሆን ለማድረግም ኤክስፖው ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። የኢንቨስትመንት ተግባራት በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው የቴክኖሎጂው ዘርፍ እድገት በኢንቨስትመንት ስራዎች ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ አለው። ኤክስፖው የቴክኖሎጂው ዘርፍ የሚተዋወቅበት በመሆኑ የኢንቨስትመንት ስራዎችን በቴክኖሎጂ ውጤቶች በመደገፍ የኢንቨስትመንት ውጤታማነትን ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል።

የቴክኖሎጂ ኤክስፖው በዘርፉ ልምድ ያላቸው ትልልቅ ኩባንያዎች ለጀማሪዎቹ ልምዳቸውን የሚያካፍሉበት በመሆኑ ጀማሪ ባለሙያዎችም አቅማቸውን እንዲያሳድጉ ትልቅ እድል ይፈጥርላቸዋል። ስለሆነም ጀማሪ የቴክኖሎጂ ተቋማት (Startup Businesses) በኤክስፖው ተሳታፊ እንዲሆኑ እንደሚደረግ አቶ ሳምሶን ተናግረዋል።

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ዳይሬክተር ጀኔራል አምባሳደር ዲና ሙፍቲ የቴክኖሎጂ እድገትና ሽግግር ለዘላቂ ምጣኔ ሀብታዊ እድገት እጅግ አስፈላጊ ግብዓት መሆኑን ጠቁመው፤ ኤክስፖው ለቴክኖሎጂ ሽግግርና ለልምድ ልውውጥ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ጉልህ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው አስታውቀዋል።

እንደአምባሳደር ዲና ማብራሪያ፣ የኢንቨስትመንት ተግባራት ቴክኖሎጂን መሰረት በማድረግ የሚከናወኑ በመሆናቸው ኤክስፖው በዘርፉ ከሚያስገኘው የኢንቨስትመንት ፍሰት በተጨማሪ ሌሎች የኢንቨስትመንት ተግባራትም ውጤታማና ቀልጣፋ እንዲሆኑ እገዛ ይኖረዋል። ከዚህ በተጨማሪም ኤክስፖው ለሀገር ገጽታ ግንባታም አወንታዊ ሚና ይኖረዋል።

በኤክስፖው ላይ የፖሊሲ አውጪዎችም ተሳታፊ ስለሚሆኑ ለቴክኖሎጂው ዘርፍ እድገት ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ ሕጋዊ አሰራሮችን ለመዘርጋት ለሚደረገው ጥረት ግብዓት ለመሰብሰብ ትልቅ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ተገልጿል። የቴክኖሎጂው ዘርፍ የዘርፉን ተለዋዋጭነት ከግምት ውስጥ ባስገቡ ግልጽ ሕጋዊ ማዕቀፎች ካልታገዘ እድገቱን መምራትና ማስተዳደር ስለማይቻል የፖሊሲ አውጪዎች በኤክስፖው ላይ መሳተፋቸው የዘርፉን አስተዳደር በሰለጠነ ሕጋዊ አሰራር ለመምራት ለሚደረገው ጥረት ቀላል የማይባል ሚና ይኖረዋል።

በኹነቱ የሚስተናገዱ ሲምፖዚየሞችም የቴክኖሎጂ ውጤቶች ያሉበትን ደረጃ ለመገምገምና በአፍሪካ አህጉር በዘርፉ ያለውን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ለመቃኘት እንደሚያስችሉ ተነግሯል። ከዚህ በተጨማሪም ሲምፖዚየሞቹ ስለቴክኖሎጂ ፖሊሲ ጉዳዮች ሰፋ ያለ ግንዛቤ የሚፈጠርባቸው መድረኮች እንደሚሆኑም አዘጋጆቹ ገልፀዋል። የመንግሥትንና የግሉን ዘርፍ ትብብር ማሳደግና የቴክኖሎጂውን ዘርፍ በፋይናንስ መደገፍ ስለሚቻልበት ሁኔታ እንዲሁም በየአካባቢው ያሉ መልካም ተሞክሮዎችን በአፍሪካ ብሎም በመላው ዓለም በማስፋት በቴክኖሎጂው ዘርፍ የተረጋጋ የስራ ሁኔታ (Better Business Certainty) እና አዳዲስ እድሎችን ለመፍጠር ምክክር ይደረጋል።

በኤክስፖው ጀማሪ ኢትዮጵያውያን የቴክኖሎጂ ባለሙያዎች ከትልልቆቹ የቴክኖሎጂ ተቋማት ልምድ እንደሚቀስሙ ይጠበቃል። የቴክኖሎጂውን ዘርፍ በማሳደግ ዘላቂ የምጣኔ ሀብት እድገት ለማስመዝገብ እነዚህን ጀማሪ ባለሙያዎች መደገፍ ያስፈልጋል።

አዲሱ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲም ጀማሪ የቴክኖሎጂ ባለሙያዎች አቅማቸውን እንዲገነቡ ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥር ማዕቀፍ ሆኖ ተዘጋጅቷል። ጀማሪ ተቋማት እና የኢኖቬሽን ሥርዓተ-ምህዳር ገንቢዎች (STI Incubation Centers) የፋይናንስ፣ የቴክኒክ፣ የመስሪያ ቦታ እና መሰል ድጋፎችን የሚያገኙበት፤ ለጀማሪ ተቋማት (Technology Startups) የገበያ ዋጋ ትመና እና የኢንቨስትመንት እድል የሚፈጠርበት፤ ስትራቴጂካዊ ተፈላጊነት ባላቸው የቴክኖሎጂ መስኮች የግልና የመንግስት አጋርነት የሚኖርበት፤ በጥናት ላይ የተመሠረተ የእሴት ሰንሰለት እና የኢኖቬሽን ክላስተሪንግ ስርዓት የሚስፋፋበት እንዲሁም ውጤታማነታቸው የተረጋገጠና ወደ ምርትና አገልግሎት የተቀየሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን የሚያበረታታ የግዥ ሥርዓት የሚዘረጋበት የአሰራር ስርዓት እንዲኖር እንደሚደረግ በፖሊሲው ላይ ተጠቅሷል።

የቴክኖሎጂ አቅም ክምችትንና የዕውቀት ሽግግሩን ለማሳለጥ ሀገርን ምርታማና ተወዳዳሪ ለሚያደርጉ ቴክኖሎጂዎች ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሰራ እንዲሁም የሀገር በቀል ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀምና ለማሳደግ የሚያስችል ስርዓት እንደሚዘረጋ በፖሊሲው ላይ ተመላክቷል። የኢኖቬሽን ሥነ-ምህዳር በመፍጠርና የሃገሪቱን የኢኖቬሽን አቅም በማዳበር ኢኖቬሽንን በሰፊው ለልማትና ሰፊ የሥራ ዕድሎችንና ሀብቶችን ሊፈጥር በሚችል መልኩ፣ በሀገርም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ መሆን የሚችሉ በርካታ ኢንተርፕራይዞችን ለመፍጠር እንደሚሰራም ተገልጿል።

ታዲያ የጀማሪ የቴክኖሎጂ ባለሙያዎችን አቅም ለማሳደግ ያስችላሉ ተብለው በፖሊሲው ላይ የተጠቀሱትን ግብዓቶች በተግባር ለመተርጎም እንዲህ ዓይነት መድረኮች የሚያስገኟቸውን መልካም አጋጣሚዎችን በሚገባ መጠቀም ይገባል።

ከአስር ዓመቱ ሀገራዊ የልማት እቅድ ስትራቴጂካዊ ምሰሶዎች (Strategic Pillars) መካከል አንዱ የቴክኖሎጂ አቅም እና ዲጂታል ኢኮኖሚን መገንባት ነው። ይህን ለማሳካት ደግሞ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፉን ውጤታማነት ማሳደግ ወሳኝ ግብዓት እንደሆነ ይታወቃል። የዘርፉን ውጤታማነት ለማጎልበት ከሚተገበሩ አቅጣጫዎች መካከል ጀማሪ የስራ ፈጣሪዎችንና የቴክኖሎጂ ባለሙያዎችን ሃሳባቸውን ወደ ቢዝነስ ተግባራት የሚያሸጋግሩባቸውን እድሎችን መፍጠር ተጠቃሽ ተግባር ነው። የአፍሪካ የቴክኖሎጂ ኤክስፖ ለዚህ ተግባር ስኬት ቀላል የማይባል አስተዋኦ ይኖረዋል። ስለሆነም ኤክስፖው የሀገር መልካም ገጽታን በመገንባት፣ የልምድ ልውውጥና የገበያ ትስስር በመፍጠር፣ ኢትዮጵያን የኢንቨስትመንት መዳረሻ በማድረግ እንዲሁም የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በማስተዋወቅ ረገድ ያስገኛቸዋል ተብለው የሚጠበቁትን እድሎች ሁሉ መጠቀም ይገባል።

አዲስ ዘመን | ማክሰኞ ነሐሴ 10 ቀን 2014 ዓ.ም



# ወቅታዊ ትንታኔ

# የሠላም ውይይት እና የህወሓት ቅድመ ሁኔታዎች አንድምታ

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

መንግስት በየትኛውም ቦታ፤ በማንኛውም ሰዓት በሰላም ጉዳይ ላይ ለመነጋገር ዝግጁ መሆኑን አስታውቃል። ይህም ብቻ ሳይሆን ድርድሩን ለማካሄድ ያግዝ ዘንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርን ጨምሮ ሌሎች ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች በመንግስት በኩል መሰየማቸው ይታወሳል። ይሁን እንጂ ህወሓት የሰላም ውይይቱ በተሳካ ሁኔታ እንዳይካሄድ አደናቃፊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን በመደርደር ላይ ይገኛል። ቀድሞም ቢሆን ለሰላም ያለው ሁኔታ የሚታወቅ ቢሆንም አሁንም ችግሮችን ሁሉ በውይይት ለመፍታት የሚደረገውን ሂደት የሚያደናቅፉ በውይይት ወቅት ሊፈቱ የሚችሉ ጉዳዮችን እንደቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ አስቀድሞ የሰላም እንቅፋት የመሆን ምልክቶችን እያሳየ ነው።

የስትራቴጂክ ጉዳዮች ተመራማሪው ዶክተር ወሂበእግዜር ፈረደ ፤ ህወሓት እና የፌደራል መንግስት በንግግርና ውይይት ሠላማዊ አማራጮችን በመጠቀም ኢትዮጵያን አንድነት ለመጠበቅ የሚደረገው ጥረት የሚደነቅና ዘመኑ የሚጠይቀው ፍልስፍና መሆኑን ይናገራሉ ። ይሁን እንጂ ውይይቱን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ሁኔታዎች ከወዲሁ እየታዩ ነው ባይ ናቸው። በመሆኑም ከህወሓት ጋር የሚደረገው ውይይት ከቀጣናው ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ፤ ከኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶችና ከሚኖራቸው ሚና፣ ከህወሓት አፈጣጠርና ባህሪ አኳያ፣ ከስተራቴጂክ ጥቅሞችና የኢትዮጵያ ዘላቂ ጥቅሞች አኳያ መመዘንና መተንተን አለበት ሲሉ ሀሳባቸውን ያካፍላሉ ።

በሁለቱ አካላት መካከል የሚደረገው ውይይት የሚወሰነው በውስጣዊ እና ውጫዊ ሁኔታዎች መሰረት በማድረግ ነው የሚሉት ዶክተር ወሂበእግዜር፤ የዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ጫና፣ የሀገሪቱ ወቅታዊና የቀጣናው ሁኔታ እንዲሁም የህወሓት አቋምና ከበስተጀርባው የሚገኙ አካላት የሚኖራቸው ሚና ቀላል እንዳልሆነ ያብራራሉ። የሠላም ድርድሩን እንደመሩና እንዲያደራድሩ ሚና ይኖራቸዋል የተባሉት አካላት መንገዶችን ሰላማዊ በማድረግ አሊያም ደግሞ ወደለየለት ችግር ውስጥ እንዲገባ ምክንያት ሊሆኑ እንደሚችሉ ይነገራሉ።

ህወሓትን ወደ ስልጣን ከማምጣት ጀምሮ እስከአሁን ድረስ ከበስተጀርባው በርካታ ተዋንያን መኖራቸውን የሚናገሩት ዶክተሩ ፤ በድርድሩ ላይም ሊኖራቸው የሚችለው ተፅዕኖ በቀላሉ የሚገመት አይደለም። በተለይም ደግሞ አፍቃሪ ህወሓት የሆኑና በጥቅም የተሳሰሩ ድርጅቶችና አካላት በድርድሩ ላይ የሚኖራቸው ሚና ቀላል አይሆንም ብለዋል።

ህወሓት ለሰላም ውይይቱ ቅድመ ሁኔታዎችን ማስቀመጡ ሁኔታዎችን በመገምገምና የረጅም ጊዜ ጥቅሙን በማስላት ጭምር ነው የሚሉት ዶክተር ወሂበእግዜር ፈረደ፤ ይህን ጉዳይ በጥልቀት መመርመርና መከታተል እንደሚገባ ይጠቁማሉ። እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎችን ለማሳካት ህወሓት ብዙ ርቀት የሚጓዝ መሆኑ መታወቅ አለበት። በውይይቱ እንደቅድመ ሁኔታ ከተቀመጡት መካከል ከሱዳን የሚያገናቸውን ኮርደር ጨምሮ ሌሎች አካባቢዎችን ከትግራይ ክልል ልዩ ሃይል ውጭ ሌላ የታጠቀ አካል መኖር የለበትም የሚል ሲሆን፤ ይህም የፌደራል መንግስትን አሰራር የሚቃረን ነው። መንግስት ለሰላም ሲል ይህን ቢያደርግ እንኳን ቀጣይ የሕወሓት ጉዞ ኢትዮጵያን ለከፋ አደጋ የሚሰጥ ይሆናል።

በተለይም በሱዳን ኮሪደር መንገድ ማስከፈት ማለት ከፍተኛ የሆነ የጦር መሳሪያን ከታሪካዊ ጠላቶች ማግኘትና የጦርነት በር በሰፊው መክፈት ሲሆን፤ ይህም ህወሓትን ጎትቶ ወደመንበረ ስልጣኑ መመለስ ማለት ነው። በመሆኑም ሕወሓት ይህን እንደ ቅድመ ሁኔታ ማስመቀጡ አግባብ ካለመሆኑም በተጨማሪ፤ ለሠላም ድርድሩ አንዳችም ፍላጎት የሌለው መሆኑን ያሳያል። ይህም ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያን ለከፋ ትርምስና መከፋፈል የሚዳርግ ታሪካዊ ሥህተት እንደሚሆን ነው ያመለከቱት ።

ሌላኛው በሰላም ውይይት ሂደት ውስጥ ህወሓት እንደቅድመ ሁኔታ ከሚያቀርባቸው ሁኔታዎች መካከል የፌደራል መንግስት ለክልሉ ገንዘብ እንደ አሸን እንዲለቅና ህወሓቶች እንደ ቀድሞው ለፈለጉት ዓላማ እንዲያውሉ



አቶ በፍርዱ ጥላሁን



ዶክተር ወሂበእግዜር ፈረደ፤

የሚል ስውር እሳቤ ያነገበ መሆኑን ይናገራሉ። ይህ ማለት ደግሞ አሁንም የህወሓትን አቅም ማጠናከርና ከሰላማዊ አማራጮች ይልቅ ጦርነት አቅሙን እንዲያጠናክር ዕድል መስጠት ነው። ከዚህም በተጨማሪ ድርድሩ በአፍሪካ ህብረት ስር መከናወን አለበት የሚለውን የፌደራሉን መንግስት ለማጣጣል እየተሄደበት ያለው መንገድና ከበስተጀርባ የታሰበው ነገር ሲሰላ እጅግ አደገኛ መሆኑ ነው። በተለይም የሰላም ውይይቱ ከአፍሪካ ህብረት አፈንግጦ እንዲወጣ እና ሌሎች የህወሓት ናፋቂዎች የድርድሩ አካል እንዲሆኑ ማድረግ ዓለም አቀፍ ጫናዎች በኢትዮጵያ ላይ እንዲበረቱ ዕድል መክፈት ስለመሆኑም ይናገራሉ።

ህወሓት ያስቀመጣቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ተፈፃሚ ለማድረግ በርካታ አካላትን የማግባባት ሥራ የሚሰራ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት መንግስት በዲፕሎማሲው ሥራ የተጠናከረ ሥራ ማከናወን አለበት። በተለይም ደግሞ ታሪካዊ የኢትዮጵያ ጠላቶች ከህወሓት ጋር ያላቸውን ሰንሰለት መበጣጠስና አካሄዳቸውን መግታት ይገባል ሲሉ ምክረ ሀሳብ ሰጥተዋል።

ዶክተሩ እንደሚሉት፤ ህወሓት ውስጣዊ እና ውጫዊ ሁኔታዎችን በመቃኘት የውይይት አማራጮችን ለመጠቀም የሚፈልግ ቢሆንም አሁንም ቢሆን ጦርነትን ዳግም ለመጀመር በሩን ዝግ አላደረገውም። በቀጣይም ትንኮሳዎችን መፈፀምና መውረር የሚለው የህወሓት ሁለተኛው አማራጭ መሆኑንም ማጤን ይገባል። በአሁኑ ወቅት ማንኛውንም አማራጭ በመጠቀም ስልጣን ለመቆናጠጥ መረብረብ የህወሓት ምኞትና አፈጣጠሩ ጭምር መሆኑም ሊታወቅ ይገባል።

ህወሓት ሀገር እየበጠበጠም ቢሆን መኖር የሚችለው በክልሉ ሰላም ሲሰፍን ሳይሆን ህዝቡ በችግርና በጦርነት እየታመሰ ሲኖር ነው። በክልሉ ሰላም ከሰፈነ የትግራይ እናቶች የሚያነሷቸው በርካታ ጥያቄዎች ስለሚኖሩና ህወሓት በክልሉ ህዝብ ተቀባይነት እያጣ ስለሚሄድ የዕድሜው ማራዘሚያ በማድረግ የሚጠቀመው ስትራተጂ ሰላም እንዳይሰፍን ማድረግ ብቻ ነው።

የህግ ባለሙያው አቶ በፍርዴ ጥላሁን በበኩላቸው፤ ህወሓት እና የፌደራል መንግስት በሠላማዊ ድርድር ወደ አንድነት ቢመጡ በማናቸውም መስፈርት ኢትዮጵያ ታተርፋለች፤ እንደቀጣናው ብዙ ትርጉሞች ይኖሩታል። በተለይም ደግሞ በህወሓት ቀንበር ሥር ተቀፍድዶ ያለው የትግራይ ህዝብ ከሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የመገናኘትና ሌሎች የፖለቲካ አማራጮች ላይም ለማማተር እድል የሚከፍትለት ይሆናል። ከዚህም በተጨማሪ በክልሉ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ለትግራይ ህዝብ አማራጭ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም እና ፍልስፍና ይዘው የሚመጡበት መንገድ የመከፈት ዕድል አለው።

ምንም እንኳን የሠላም ውይይቱ ዘርፈ ብዙ ፋይዳዎች ቢኖሩትም ህወሓት በዚህ መንገድ ሀቀኛ ሆኖ ይወያያል የሚለው ግን አጠያያቂ ሆኗል ባይ ናቸው። በተለይም ህወሓት ለዘመናት የኢትዮጵያን ፖለቲካ ሲዘውር በነበረበት ዘመኑ በርካታ ማህበራዊ፤ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶችን በመፍጠሩ ዳግም ወደ መንበረ ስልጣኑ የመመለስ ዕድል የሌለው በመሆኑ ድርድሩ እንዳሰበው ውጤት ላያመጣለት ይችላል። ከዚህም በተጨማሪ በአማራ እና አፋር ክልሎች ወረራ በፈፀመበት ወቅት ሲፈፅማቸው የነበራቸው ግፎች ከህግ ተጠያቂነት የሚያስመልጠው ባለመሆኑ ይህም ሌላኛው ራስ ምታቱ ነው።

ህወሓት በተደጋጋሚ ሲፈፅማቸው የነበሩትን ጥፋቶችን ከማረም ይልቅ በተደጋጋሚ በጥፋት ላይ ጥፋት በማወጅና ሥውር መንገዶችን በመከተል ዘመናትን ተሻግሯል። ይህን አካሄድ ለማለሳለስም ሆነ ሠላማዊ አማራጮችን ለመምረጥ አሊያም ደግሞ ሰጥቶ መቀበል የሚለውን መርህ የመቀበል ሞራል የሌለውና ሀገራዊ አንድነት የሚባለው ነገር ብዙም የማይዋጥለት ቡድን ስለመሆኑም የኋሊት ታሪኩን መሰረት በማድረግና ባህሪውን በመተንተን አደገኛ አካሄድ የሚከተል ቡድን ስለመሆኑም ይናገራሉ።

እንደ ህግ ባለሙያው ከሆነ፤ በዚህ ድርድር ውስጥ ህወሓት የሚፈልጋቸውን በርካታ ነጥቦችን ማስቆጠርና የፌደራል መንግስት የጥፋቱን ከፍተኛ ድርሻ እንዲወስድ አማራጮችን መጠቀም ነው። ለዚህም ሲባል የሰላም ውይይቱን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ቅድመ ሁኔታዎችን አስቀምጧል።

ህወሓት እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች ለማስቀመጥ የፈለገው በሂደት አገኛለሁ ብሎ ለሚያስበው የፖለቲካ ልዕልና ዋነኛ መንገዶች ናቸው ብሎ በማሰብ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በቀጣይ ወደ ስልጣን ለመምጣትና የበቀል ዕርምጃዎችን ለመውሰድም የጥርጊያ መንገድ አድርጎ ያስባል። በተለይም ደግሞ የፌደራል መንግስቱን ልዕልና እና ስልጣን ላለመቀበል የሚያደርጋቸው ጥረቶች በህግ መንግስቱም ሆነ በየትኛውም የዓለም ፖለቲካ መመዘኛ አግባብነት የጎደለው ነው። ሆኖም የውጭ ኃይሎች ድጋፍ፣ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶችና ውስጥ ባንዳዎችን በመጠቀም ዓላማውን የሚያሳካ የሚመስለው በመሆኑ በውይይቱ ላይ አያሌ ነጥቦችን ለመዘርዘር ተገዷል። ምንም እንኳን በቅድመ-ውይይቱ በህወሓት በኩል የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች እንደማይሳካላት ቢያውቅም ባለችው አቅም የመደራደሪያ ነጥቦችን ለመፍጠር ሁኔታዎችን ለማየት መገደዱ አይቀሬ ነው ባይ ናቸው።

ህወሓት ድርድሩን በተቻለ መጠን ማፋረስ ዓላማው መሆኑን የሚናገሩት አቶ በፍርዴ፤ ድርድሩ በፈለገው መንገድ ቢሳካለትና ሠላማዊ መንገድ ክልሉን እንዲያስተዳድር ቢፈቀድለትም አቅምና የሞራል ብቃት የሌለው መሆኑን ይናገራሉ። በተለይም ደግሞ ልዩነቶችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት ሲቻልና ከፌደራል መንግስት ጋር ያለውን ልዩነት ማጥበብ የሚችልበት ሰፊ ዕድል እያለ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የትግራይ ዜጎችን ለከፋ አደጋ ማጋለጡ በአሁኑ ወቅት የእግር እሳት ሆኖበታል። በመሆኑም ዳግም ክልሉን የማስተዳደር አቅምና እድል ቢያገኝም እንደ ቀድሞ ተቀባይነት የሌለው ቡድን በመሆኑ ይቸገራል። በመሆኑም የሠላም ውይይቱ ላይ ሊቀመጡ የማይገቡ ነጥቦችን በማስቀመጥ የማሰናካል ፍላጎት አለው። ይህም ብቻ ሳይሆን አደገኛ የሰላም የውይይት ሂደት በመከተል የፌደራል መንግስት ዳተኛ ነው ብለው ዳግም ህዝብን ለመቀስቀስና ወደ ጦርነት ለመማገድም ብዙ ጥረት ሊያደርጉ እንደሚችሉም ይጠቁማሉ።

ምሁራኑ እንደሚሉት፤ ህወሓት የመጣባቸው መንገዶችና ሊሄድባቸው የሚወጥናቸው ንድፎች አሁን ያለው ነባራዊ የኢትዮጵያ ሁኔታ ዕድል ስለማይሰጠው በሠላም ውይይት ሂደት ላይ በርካታ እንቅፋቶችን እንደሚፈጥር መገመት ይቻላል። የክልል መንግስት ሆኖ የፌደራሉን መንግስት የሚገዳደር ፈርጣማ አቅም ያለው ቡድን ለመምሰልና የውጭ አካላትን ይሁንታና ዕይታ ለማግኘት ጥረት የሚያደርግ ይሆናል። በመሆኑም መንግስት ዓለም አቀፍ ማህበረሰቡን በማሳመንና የህወሓትን ቡድን የጥፋት አካሄድ በማጋለጥ በዲፕሎማሲው ትልቀ ሥራ መሥራት ይጠበቅበታል። ከዚህም በተጨማሪ ህወሓት ድርድር በሚለው ሐሳብ ሰጥቶ የመቀበልን መርህ የማይከተል በመሆኑ ቡድኑ ያስቀመጣቸው ቅድመ ሁኔታዎች ካልተሳኩ ዳግም ጦርነትና ወረራ መፈፀም ሁለተኛው አማራጭ ነው። ይህም በመሆኑ የፌደራል መንግስት ከወዲሁ ከፍተኛ ጥንቃቄ እና ዝግጅት ማድረግ እንዳለበትም ያሳስባሉ።

ሙሁራኖቹ በሰጡት የመፍትሄ ሀሳብ አሁን ህወሓት ያስቀመጠው ቅድመ ሁኔታ የትግራይን ህዝብ ለመጥቀም ሳይሆን በክልሉ ሰላም እንዳይሰፍን ፤ ህዝቡም ተረጋግቶ ሰላማዊ ኑሮውን መምራት እንዳይችል እንቅፋት ለመሆን ነው ።ይህንን የሚያደርግበት ዋናው ምክንያትም በክልሉ ሰላም ከሰፈነ የህዝቡን ጥያቄ መመለስ እንደማይችል ያውቀዋል፤ ተቀባይነትም አይኖረውም የሚቋምጥለትን ስልጣን አያገኝም። ስለዚህ ሁልጊዜ ሰላምን እያደፈረሰና በሀሰተኛ ፕሮፓጋንዳው ዓለማቀፉን ማህበረሰብ እያታለለና የክልሉን ህዝብ በችግር እያሰቃየ መኖርን ይሻል። በመሆኑም መንግስት የጀመረውን የዲፕሎማሲ መንገድ አጠናክሮ መቀጠል አለበት።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# በበጎ ፍቃድ የታበሱ እንባዎች

**ሰላማዊት ውቤ**



ወይዘሮ እልፍነሽ ባሉ



ወይዘሮ ጀሚላ አሽረቅ



ወይዘሮ አይሻ አወል



ወይዘሮ ፋንታዬ አትርፉ



ወይዘሮ ዛፈነሽ አባገ

‹‹ልጆቼ እንደምታዩኝ ዕድሜዬ ገፍቷል። አቅሜም ደካማ ነው ።የዘንድሮ ክረምት ደግሞ እጅግ ኃይለኛ ነው። እንዳለፉት ዓመታት ልብስ መዘፍዘፊያ እየደቀንኩ፤ በታች በበር የሚገባውን ደግሞ በቁም መጥረጊያ በመመለስ ፍፁም ልከላከለው አልችልም›› ይህ ድምጽ የተሰማው ከወይዘሮ እልፍነሽ ማዘንጊያ ነው።

ወይዘሮ እልፈነሽ በአረጀ እና በተጎሳቀለ ቤት ውስጥ ለዘመናት ኖረዋል። በበጋ ንፋሱና ጸሃዩ በክረምት ደግሞ ጎርፍና ጻሃዩ ሲያንገላታቸው ዘመናትን ተሻግረዋል።

የቀለም ትምህርት መቅሰም ባለመቻላቸው ዕድሜያቸውን በውል ባያቁትም አፄ ኃይለስላሴ ሲመለሱ ነው ጅባትና ሜጫ ውስጥ የተወለድኩት የሚሉት እኝህ እናት አሁን ላይ መሳለሚያ አካባቢ በቀበሌ ቤት ውስጥ ትዳር ይዘው መኖር ከጀመሩ ከ40 ዓመታት በላይ ማስቆጠራቸውንም ያወሳሉ።

በእነዚህ አመታት ወይዘሮ እልፍነሽ መከራና ጉስቁልና ተፈራርቀውባቸዋል። እንደ ሰው ባማረ ቤት ውስጥ መኖር ቢመኙም በዳሳ ቤት ውስጥ ከመኖር የገላገላቸው አልነበረም። በቤታቸው ጉስቁልና ስለሚሸማቀቁም የቅርብ ዘመድና ወዳጅ እንኳን መጥቶ እንዲጠይቃቸው አይፈቅዱም ። ገመናቸውን ሸሽግ አድገው ከሰው ተከልሎ መኖር ነው ምርጫቸው።

በግል ጫማ ቤት እየሰሩ ሲያስተዳድሯቸው የነበሩት ባለቤታቸው እንደዛሬ አቅማቸው ሳይደክም ቆርቆሮ ከመቀየር ጀምሮ ቤቱን በተለያየ ደረጃ ሲያድሱት መኖራቸውንም ያነሳሉ።

አሁን ላይ እሳቸውን ጨምሮ ባለቤታቸውንና አንዷ በሽተኛ ልጃቸው የሚተዳደሩበት ምንም ገቢ የላቸውም።ስለዚህም ቤቱ እላያቸው ላይ ሲፈርስ ከማየት ውጪ አማራጭ አልነበራቸውም።

ሆኖም መቆየት ደጉ ዛሬ ነገሮች ተለውጠዋል። በወይሮ እልፍነሽ ደጃፍ ጸሃይ መውጣት ጀምራለች። መንግስት በየአካባቢው ያስጀመረው የበጎ ፍቃድ ስራ ችግራቸውን ገፎላቸዋል። ለዘመናት ያዘመመ ጎጇቸው ቀና ብሎ ግርማ ሞገስ ተላብሷል። በማራኪ ሁኔታ ታድሷል። በወይዘሮ እልፍነሽ ፊትም ላይ ደስታና ተስፋ ይነበባል።

ቤታቸው አሁን በበጎ ፈቃድ አገልግሎት በተሰማሩ ወጣቶችና በአካባቢው ሕብረተሰብ ትብብር ተሰርቶላቸዋል።

ሌላዋ የዚሁ መሳለሚያ እህል በረንዳ አካባቢ ነዋሪ እናት ወይዘሮ ጀሚላ አሽረቃ ናቸው። ቤቱ በላዬ ላይ ሊደነባ(ሊፈርስ) ትንሽ ነበር የቀረው የሚሉት እኝህ እናት ባለፉት በርካታ ክረምቶች ከላይ የሚወርደውን ዝናብ ማስታጠቢያ በመደቀን ለመከላከል ብዙ ሌሊቶችን ቆመው ማሳላፋቸውን ይናገራሉ።

የዘንድሮ ክረምት ደግሞ እጅግ ከባድ ነው።በመደቀን ብቻ የሚከላከሉት አልሆነም። እንኳን በውድ ዋጋ ቆርቆሮ፤ እንጨትና ምስማር ገዝቶ ማደስ ቀርቶ ከነልጆቻቸው የዕለት ጉርስ የላቸውም። ሲደግፏቸው የነበሩትን ባለቤታቸውን በሞት ከተነጠቁ ዓመታት ተቆጥረዋል።

የሃምሌ ወር ዳዙን ሰብስቦ እያስገመገመ ሲመጣ ወይዘሮ ጀሚላ እንዴት እሆን ይሆን ብለው ሃሳብ ገባቸው። ክረምቱ መግቢያ አካባቢ እርጥባን ሰብስበው ላስቲክ ሸራ ቢያስለብሱትም ፈጽሞ ሊመክተው አልቻለም። የሰኔውም ሆነ የሐምሌው ዝናብ ላስቲክ ሸራውን ብጥስጥሱን አወጣው።የወይዘሮ ጀሚላ ገመና ሊጋለጥ ሆነ። በሃምሌ ጨለማ ከነስምንት ልጆቻቸው የጎዳና ሲሳይ መሆናቸው አሳሰባቸው።

ሆኖም ሳይደግስ አይጣላም እንደሚባለው አለሁልሽ የሚሏቸው ወገኖች ደረሱላቸው። የበጎ ፍቃድ የሚሰጡ ወጣቶች እንባቸውን አበሱላቸው። ከነስምንት ልጆቻቸው በላያቸው ላይ ሊፈርስ ያዘመመውን ቤት ደርሰው አቀኑት። አቧራውን አራግፈው በብሎኬት አደሱት። የዘመመውም ህይወት ቀና አለ። በወይዘሮ ጀሚላ ቤት ደስታ ነገሰ።

ሌላኛዋ እናት ወይዘሮ አይሻ አወል ናቸው። አዲስ አበባ መኖር ከጀመሩ 16 ዓመታትን አስቆጥረዋል።የስድስት ልጆች እናት ናቸው። ስድስተኛውንና የመጨረሻ ልጃቸውን የወለዱት ክረምቱ መግቢያ አካባቢ ነበር። ቤቱ ቀድሞ በመፍረሱ የአካባቢው ሰው ሸራ ጋርዶላቸው ነው የአራስነት ጊዜያቸውን ያሳለፉት። ሆኖም ሸራውን የዘንድሮ ክረምት ዝናብና ዶፍ አሸነፈውና በላያቸው ላይ ሊፈረስ ተቃረበ። ከእርሳቸው ይልቅ ያሳሰባቸው የአራስ ልጃቸው ጉዳይ ነበር። ገና በጨቅላ ዕድሜው በብርድ ተጎድቶ እንዳይሞት ወይም ቀሪውን ህይወቱን በበሽታ እንዳያሳልፍ ሰጉ። የክረምቱን መግባት በስጋት ተመለከቱት። ሆኖም ኢትዮጵያ የደጋጎች ሀገር ነችና ስቃይና መከራቸውን ያዩ አንዲት በጎ አድራጊ ወይዘሮ አይሻን ከስጋት ገላገለቻቸው። በጥሩ ሁኔታ ቤታቸውን አድሰው አስረከቧቸው።

ወይዘሮ አይሻም ለተደረገላቸው በጎ ስራም የሚከፍሉት ነገር ባይኖራቸውም ‹‹ አላህ በድራቸውን ይክፈልልኝ ፤እኔማ ምን አቅም አለኝ›› በሚል በጎ ሰሪዋን አመስግነዋል።

የክረምት በጎ ፍቃድ ስራ በርካታ ሴቶችን ተጠቃሚ እያደረገ ነው። በበርካታ ውስብስብ ችግሮችና ድህነት ውስጥ ለሚኖሩት ሴቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት እፎይታ እየሰጣቸው ነው።

ወይዘሮ ፋንታዬ አትርፉ በመሳለሚያ እህል በረንዳ አካባቢ ሰላም ሰፈር እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪ ናቸው።እንደነገሩን የእሳቸውን ቤት ጨምሮ በዚህ አካባቢ የነበሩት የቀበሌ ቤቶች በሙሉ በእርጅና ምክንያት ወድቀው የነበሩ ናቸው። አብዛኖቹ ቤቶች የቀበሌ ቤቶች በመሆናቸው በጣም ያረጁና የተጎሳቀሉ ናቸው። የቤቶቹ ባለቤቶችም ከእጅ ወደ አፍ ኑሮን የሚገፉ በመሆናቸው ቤት ማሳደስ ቀርቶ የዕለት ጉርሳቸውን ሸፍኖ ማደር እንኳን አቅም የላቸውም።

ብዙዎቹም በአካባቢው የሚገኙ ቤቶች እንደሳቸው ቤት ሁሉ አራት በአራት የሆኑ ጠባብ ቤቶች ናቸው። መተኛውም፤ማብሰያውም ፤መብያውም ፤ማጠቢያውም ያችው አንዲት ክፍል ነች። ወይዘሮ ፋንታዬ የወታደራዊው ደርግ አስተዳደር መንግስት ወደ ስልጣን ሲመጣና የግለሰብ ቤት ተከራዮችን ባላችሁበት እርጉ የሚል አዋጅ ሲያውጅ በወሰነው የኪራይ ታሪፍ መሰረት ላለፉት አርባ አመታት ለቀበሌ ሲከፍሉ ኖረዋል። ሆኖም ለረጅም ጊዜ በዚህ ሁኔታ ቢኖሩም ቤታቸው በላያቸው ላይ እስኪወድቅ ድረስ ያያቸው አንድም አካል አልነበረም።

እሳቸውም ቤታቸውን እንዳያድሱ ከእርሳቸውንና ከልጆቻቸው የሚተርፍ ሳንቲም አልነበራቸውም። ይደግፏቸው የነበሩት ባለቤታቸው ከሞቱባቸው በኋላ በተለይ ከልጆቻቸውና ከአካባቢው ሰው ተደብቀው ልብስ ከማጠብና አሻሮ ከመቁላት ጀምሮ የተለያዩ ሥራዎች እየሰሩ የዕለት ጉርሳቸውን ሲያሚሉ ኖረዋል። ቤታቸውንም ቆርቆሮ እየቀያየሩ ሲያድሱና ቤተሰባቸውን ሲያስተዳድሩ ቆይተዋል። ይሄን ያየችው ልጃቸው ትምህርቷን ከሰባተኛ ክፍል አቋርጣ ወደ ቤሩት በመሄድ ጥሪት ቋጥራ መጥታ ቤታቸውን በተለየ ሁኔታ ሰራችላቸው።

ሆኖ የኔ ቤት ተሰርቷል ብለው ዝም አላሉም። በየዓመቱ በክረምት በአካባቢው ባሉ ቤቶች ላይ የሚደርሰውን ችግር ከማንም በበለጠ እሳቸው ስለሚያውቁትና ስለደረሰባቸው አቅማቸው በፈቀደ መጠን ለነዚህ ቤቶች እንዲታደሱ ጥረት ያደርጋሉ። ጥረታቸው ወጣት ልጆቻቸው በቤቶቹ ግንባታ እንዲሳተፉ ከመገፋፋት ይጀምራል። የእሳቸውም ቤት ምንም ያህል አንዲት ክፍልና ጠባብ ብትሆንም ጎረቤቶቻቸውን ቤታቸው ተሰርቶ እስኪያልቅላቸው ድረስ እሳቸው ጋር እንዲያርፉ ያደርጋሉ።

ሁሉም የአካባቢው ነዋሪዎች የኢኮኖሚ አቅም ከእጅ አይሻል ዶማ እንዲሉት ዓይነት በመሆኑ ከዚህ በዘለለ የሚደጋገፉበት ሁኔታ የለም።አሁን ላይ እሳቸው የሚተዳደሩት በእንጀራ ንግድ ነው።የእንጀራ ንግድ ደግሞ 100 ኪሎ ጤፍ ስድስት ሺህ ብር እየተገዛ ቢሰራም አዋጭ አይደለም። ቢያዋጣ በሚል ሩዝ ጨምረው ነው የሚጋግሩት። እንዲህ ሆኖ ገበያ ካለ በቀን ስድሳ ከሌለ 30 እንጀራ ቢጋግሩም የመብራት ፍጆታው ከፍተኛ በመሆኑና በየወሩ እስከ ሦስት ሺህ ብር ስለሚከፍሉ ትርፉን ይበላዋል። ሆኖም በሰፈራቸው ባዩት በጎ ስራ ደስተኛ ስለሆኑ ችግርን ሁሉ በትብብር እንደሚያልፉት እርግጠኛ ናቸው።

ወይዘሮ ዛፌነሽ አዛገ ይባላሉ። ወይዘሮዋ በበጎ ፈቃድ ሥራ በማስተባበሩም ሆነ ራሳቸው በተግባሩ በመሳተፉ አብዝተው ይታወቃሉ ። በቀያቸው ያሉትንና በእርጅና ምክንያት ያዘመሙ የሦስት አቅመ ዳካማ ነዋሪዎች ቤት እንዲሰራላቸው ታች ላይ ሲሉ ነው የከረሙት ። እኛ ወደ እነ ወይዘሮ ዛፌነሽ ጊቢ ስንሄድ ሩጫቸው ተሳክቶላቸውም በእሳቸው አስተባባሪነት የሶስቱም አቅመ ደካሞች ቤቶች ሲገነቡ ነው የደረስነው። ቤቶቹ ሙሉ ለሙሉ ፈርሰው ፤የጭቃ ግድግዳቸው ተደርምሶ በብሎኬት ተቀይሯል። ቤቶቹ ከቆርቆሮ መዝጊያ ወደ ብረት መዝጊያ ተለውጠዋል።

ወይዘሮ ዛፌነሽ በመጠኑም ቢሆን ስለ ሦስቱ ነዋሪዎች ስላሉበትና ስለነበሩበት ሁኔታ አጫውተውን ነበር ።የአንደኛው ቤት ባለቤት ወይዘሮ እልፍነሽ ረጅም ዕድሜ ያላቸው አቅመ ደካማ ናቸው። የአስምም ታማሚ በመሆናቸው ሽታና እርጥበት በሽታቸውን ይቀሰቅስባቸዋል። ሆኖም ቤታቸው በእርጅና ምክንያት ለረጅም ጊዜ በመውደቁ ብዙ ክረምቶችን በዚህ ሁኔታ ለማሳለፍ ተገድደው ቆይተዋል። ዘንድሮ ግን ሙሉ በሙሉ በመፍረሱ እሳቸው የአካባቢውን ሕብረተሰብ በማስተባበር በብሎኬት እንዲገነባላቸው አድርገዋል።

የአይሻና የሦስቱ ወላጅ አልባ ልጆች መኖርያ ቤትም እንዲሁ ከእርጅና ብዛት ወድቆ ነበር። በተለይ በሶስቱ ወላጅ አልባ ልጆች መኖርያ ቤት ውስጥ ጎርፍ ይገባ ነበር። ጎርፉ የመፀዳጃ ቤት ፍሳሽ የተቀላቀለበት በመሆኑ ለጤና በእጅጉ አደገኛ በመሆኑ አስተባብረው ሊያሰሩላቸው በቅተዋል።መፀዳጃ ቤቱ አርማታ ተደርጎ በስነስርዓት ዳግም የልጆቹ ችግር በማይሆንበት ሁኔታ እየተገነባ ይገኛል።

ወይዘሮ ሕይወት በቀለ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ የአካል ጉዳተኞችና የአረጋዊያን ማስተባበርያና መከታተያ ዳይሬክቶሬት ዳሬክተር ናቸው። ቢሮው ከተሰጠው ተግባር አንዱ እንዲህ እንደ መሳለሚያ እህል በረንዳ የዘንድሮው የክረምት ወራት የወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ስምሪት መርሐ ግብር የነዚህን የሕብረተሰብ ክፍሎች በተለይም የአረጋዊያን እናቶችንና የአቅመ ደካሞችን ቤት በመጠገን ሙሉ በሙሉ አፍርሶ በመሥራት ከፍተኛ አስተዋጾ ማድረጉን ይናገራሉ።

አሁን ላይ ከክረምት በጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት በተጨማሪ የሕብረተሰቡ በግልም በጋራም የመረዳዳት ባህል እየዳበረ መምጣቱን ያስታወሱት ወይዘሮ ህይወት በዚህም ስር የሰደደው የድህነታችንና ኋላ ቀርነታችን አሻራ የሆኑ ያረጁ የአቅመ ደካማና የአረጋዊያን ቤቶችን በማደሱ ረገድ ሕብረተሰቡ በግልና በጋራ ከፍተኛ አስተዋጾ እያበረከተ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ አድነው አበራ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት እንደ አገር እየጎለበተ መምጣቱ ለማህበራዊ ችግር ተጋላጭ የሆኑ ሴቶችን ችግር ለመቅረፍ ዓይነተኛ መሣርያ እየሆነ መምጣቱን አውስተዋል። በተለይ በዚህ በኩል ያለው የክረምት የወጣቶች በጎ ፈቃድ አገልግሎት ድርሻ ያረጁ ቤቶችን ከማደስና እንደገና ከመገንባት ባሻገር በችግኝ ተከላው፤ በአካባቢ ጽዳቱ፣ በጓሮ አትክልቱ በጓሮ አትክልቱና በተለያዩ የልማት መስኮች ጭምር ውጤት መገኘቱን ይናገራሉ።

የዘንድሮው የክረምት ወራት የወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ስምሪት መርሐ ግብር አረንጓዴ አሻራን ለማኖር ከሚያስችለው የችግኝ ተከላ መርሐ ግብር በተጓዳኝ 18 ሚሊዮን ወጣቶችን በተለያዩ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መስኮች ላይ በማሰማራት የማኀበረሰቡን ማኀበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን እየቀረፉ መገኘታቸውንም አቶ አድነው አንስተዋል።

እኛም ዜጎች ውስጣቸው ከሚሰማቸው ሰብዓዊ አመለካከት ተነስተው እንደ አገር ለማህበራዊ ችግር ተጋላጭ ለሆኑ እናቶች እየተደረጉ ያሉት ድጋፎች ተጠናክረው ይቀጥሉ እያልን ጽሁፋችንን በዚሁ እንቋጫለን።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

በዛሬው አዲስ ዘመን ድሮ ዓምዳችን ከ50 ዓመት በፊት የታተሙት ጋዜጦች ቃኝተናል። ለትውስታ ያህል በርካታ አመታትን መለስ ብለን ከተመለከትናቸው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዘገባዎች መካከል ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በአውሮፓ ተወዳድረው ያገኙትን ስኬት፤ አበበ ቢቂላ በውድድሩ በቼኮዝላቫኪዊ ለ11 ዓመት ተይዞ የነበረ ክብረ ወሰን መስበሩን የሚያስታውሱ ይገኙበታል። በወቅቱ በ 800 ሜትር ሩጫ ኢትዮጵያዊው አትሌት ሠይድ ሙሳ 2ኛ መውጣቱን ዝነኛው ጋዜጠኛ ሰለሞን ተሰማ ያጠናከራቸው ዘገባዎች ያሳያሉ። በወቅቱ ከተዘገቡ ወንጀል ነክ እና ማኅበራዊ ጉዳዮችንም አካተናል።

### ፫ቱ የኢትዮጵያ አትሌቶች

ሦስቱ የኢትዮጵያ አትሌቶች አበበ፣ ማሞና ሠይድ በአውሮፓ ውስጥ ማለት በስዊድን፤ በምዕራብ ጀርመን፤ በዴንማርክ፤ በኖርዌይና በቤልጅግ አገሮች ላይ እየተዘዋወሩ የኢንተርናሽናል ውድድር በማድረግ ፤፯ ሳምንት ከቆዩ በኋላ፤ ባለፈው ሳምንት አ/ አበባ መግባታቸው ቀደም ብሎ ተገልጿል።

የነዚህ አትሌቶች አሠልጣኝና መሪ ሆነው አብረው የሔዱት ሜጀር አኒ ኒሰካል ግንቦት ፳፰ ቀን በስዊድን አገር ማልም በተባለው ስታዲየም ላይ በተደረገው በየአንድ ሰዓት ሩጫ ሲናገሩ አበበና ማሞ ከመጀመሪያ ጀምረው እስከ ፲፯ኛው ኪ/ሜትር ድረስ አብረው ከሮጡ በኋላ አበበ መሪነቱን በመያዝ በተባለው ሰዓት ውስጥ ፳ ኪ/ሜትር ከ፪፻፳፯ ሜትር በመሮጥ ፩፻ ሜትር ያህል ቀድሞ ሲገባ ማሞ ደግሞ ፳ ከዜሮ ፺፯ በመሮጥ ተከትሎ ደርሷል። ፫ኛው ዴጊ ቶርነር ሶን የተባለ የዴንማርክ ተወላጅ ነው።

በአበበ የተቀደመው ፳፻፵፫ ሜትር እርቀት ሲሆን፣ ፬ኛው ምዕራብ ጀርመን ናቸው። የዚህን ርቀት ሪኮርድ ለ፲፩ ዓመት የያዘው የቼኮዝላቫኪያዊያን ተወላጅ የዛቶፔክን እርቀት አበበ በአንድ መቶ ሰባ አራት ማሞ በአራት ሜትር እርቀት እንደሰበሩ ሜጀር ገልፀዋል።

እንዲሁም በዚሁ አገር በተደረገው የ ፰፻ ሜትር ሩጫ ፩ኛ ሄርበርት ሚሲኦላ ምዕራብ ጀርመን ጊዜው ፩ ደቂቃ ከ፵፪ ሰኮንድ ነጥብ ፪

፪ኛ ሠይድ ሙሳ ኢትዮጵያ በሦስት ነጥብ ተቀዳሚነት

፫ኛ ከርት ክርስቲአንሰን ዴንማርክ ፤

፬ኛ ኤስ ኦ ኦቲሰን ስዊድን፤

ሜጀር አኒ ዜግነታቸው ስዊድን ዕድሜያቸው ፵፩ ወደ ኢትዮጵያ ከመጡ ፲፯ ዓመት አሁን የሚሠሩት በኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ዋና ጸሐፊነት ሲሆን ለኢትዮጵያ አትሌቶች በአማተር ስም የሰጡት ትህምርታዊ አገልግሎት ከፍ ያለ ለመሆኑ አትሌቶቹ ያገኙት ውጤት ምስክራቸው ለመሆን ይችላል።

ሰለሞን ተሰማ

(ሐምሌ 12 ቀን 1954 ከወጣው አዲስ ዘመን)

### መቶ ሐምሳ ሺህ የባህር ዛፍ ችግኝ ተተክሏል

ጐንደር፤ሐምሌ ፴ ቀን ፶፬ ዓ.ም የጐንደር ከተማ ከንቲባ የተከበሩ ደጃዝማች አርአያ ዋሴ ለከተማው ልማትና ለሕዝብ ምቾት ሲሉ በጐንደር አጠገብ በሚገኘው ተራራ ላይ በአዘጋጁት የተክል ሥፍራ፤ክቡር ሌተናል ጄኔራል ነጋ ኃይለሥላሴ የበጌምድርና የስሜን ጠቅላይ ገዥ በተገኙበት የከተማው ሕዝብ የፖሊስና የጦር ሠራዊት ወታደሮች የመንግሥት ሠራተኞች ፤ካህናቶችም ሳይቀሩ በበጎ ፈቃዳቸው በአንድ ኅብረት በመተባበር በዚሁ ቀን አንድ መቶ አምሳ ሺህ የባህር ዛፍ ችግኝ ተተክሎ ውሏል ሲል ወኪላችን ገልጿል።

(ነሐሴ 2 ቀን 19 54 ዓ.ም ከወጣው አዲስ ዘመን)

### ‹‹ባርቆብኝ ገደልኩት››

አበራ በቀለ የተባለ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ባልደረባ ነሀሴ ፲፮ ቀን ትናንት ከቀኑ ፮ ሰዓት ከ፵፰ ደቂቃ ሲሆን ፤ለገሠ አደራ የተባለ ባልንጀራው እቤቱ መጥቶ ፤ለሽጉጥህ ጥይት ገዛህለት ወይ ብሎ ጠይቆኝ አዎን ገዝቼለታለሁ ብዬ መኝታ ቤቴ ውስጥ ገብተን ሽጉጡንና ጥይቱን ስናይ፤በድንገት ሽጉጡ ባርቆብኝ ገደልኩት ሲል እጁን ለ፪ኛ ፖሊስ ጣቢያ የሰጠ መሆኑን የ፪ኛ ፖሊስ ጣቢያ አዛዥ ሻምበል አጥናፉ ወርቅነህ በሰጡት ወሬ አረጋግጠዋል።

(ነሐሴ 17 ቀን 1954 ከወጣው አዲስ ዘመን)

### ከጅብ አፍ ተረፈች

ሰኔ ፳፯ ቀን ፶፬ ዓ.ም. ለ፳፰ አጥቢያ ወላይታ ሶዶ ከተማ ከተማ ፩ኛ ወታደር ተፈራ ገብሬ ቍጥር 1135 ፪ኛወታደር ብርሃኑ ሽመና ቍጥር 1191 የአውራጃው ፖሊስ አዛዦች ከላይ በተጠቀሰው ሌሊት የፍተሻ ማለት የፀጥታ ሥራቸውን በአውራጃው ውስጥ ሲያከናውኑ እመት በቱሬ አሜቴ የተባለች ሴት ማታ ወደ ውጭ ወጥታ ሳለች ጅብ ይዞአት ስለጮኸች ለዕርዳታው ከላይ የተጠቀሱት ወታደሮች ደርሰው ከተናጣቂው አውሬ አትርፈዋታል። ነገር ግን በሐኪም ስለተረዳች ለሕይወቷ አያሰጋትም።

የአውራጃው አዣንስ

( ጳጉሜ 1 ቀን 1954 ከወጣው አዲስ ዘመን)


### 17 በጐች ሲነዳ ተያዘ

ወልደ ማርያም ኃይሌ የተባለ ሰው ፪ ራሱን ሆኖ ነሐሴ ፲፮ ቀን ትናንት ከቀኑ ፱ ሰዓት ላይ በእንጦጦ ወረዳ ኪዳነ ምሕረት ቀበሌ ፲፯ በጐች እየነዳ ሲሔድ፤ ኰሎኔል ፋንታ ወልደ ገብርኤል አግኝተውት በጥርጣሬ በጐቹን ከየት እንዳመጣ ቢጠይቁት የእርሱ አለመሆናቸውን ስላረጋገጠ ፤ወልደ ማርያምና ግብረ አበሮቹ፤እንዲሁም ፲፯ ቱ በጐች በ፪ኛ ፖሊስ ጣቢያ ስለሚገኙ ፤ለበዓለ ፍልሰታ በጐች አዘጋጅታችሁ የተሠረቀባችሁ ሰዎች ብትኖሩ ማስረጃችሁን እያቀረባችሁ ከጣቢያው ልትወስዱ ትችላላችሁ በማለት የጣቢያው አዛዥ ባወጡት ማሳሰቢያ ገልጠዋል።

(ነሐሴ 17 ቀን 1954 ከወጣው አዲስ ዘመን)

# ዓለም አቀፍ

## በሱዳን በተከሰተ ጎርፍ ከ50 በላይ ሰዎች ሞቱ



የክረምቱ ወቅት ከጀመረ በኋላ ባለው ጊዜ ሱዳን ውስጥ ከ50 በላይ ሰዎች በከባድ ዝናብና ጎርፍ ሳቢያ ሕይወታቸው መጥፋቱን መንግሥትና የዕርዳታ ተቋማት አሳወቁ።

ካለፈው ግንቦት ጀምሮ በአገሪቱ ውስጥ በተከሰተው ጎርፍና ከባድ ዝናብ የተነሳ 136 ሺህ የሚደርሱ ሰዎች ለችግር የተዳረጉ መሆናቸውንና በርካታ ሰዎች ለሞትና ለአካል ጉዳት ተዳርገዋል ሲል የሱዳን መንግሥት የሰብአዊ ዕርዳታ ኮሚሽን ገልጿል።

ከባድ ዝናብና ጎርፍ በሰውና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሱን ያመለከተው ኮሚሽኑ፣ በዚህም ባለፉት ወራት ውስጥ 52 ሰዎች ሲሞቱ 25 ሰዎች ደግሞ ጉዳት ደርሶባቸዋል።

በተጨማሪም ጎርፉ በ12 የአገሪቱ ግዛቶች ውስጥ ስምንት ሺህ 900 የሚሆኑ ቤቶችን ያወደመ ሲሆን በሌሎች 20 ሺህ 600 ቤቶች ላይ ደግሞ የተለያየ መጠን ያለው ጉዳት አድርሷል።

በጎርፍ ጉዳት ከደረሰባቸው ግዛቶች መካከል ከፍተኛው ሞት የተመዘገበው በሰሜን ኮርዶፋን ሲሆን በግዛቷ 19 ሰዎች ሞተዋል።

በተከታይነት ደግሞ በናይል ሪቨር ግዛት ውስጥ ደግሞ ሰባት ሰዎች መሞታቸውን የሱዳን ብሔራዊ የሲቪል መከላከያ ምክር ቤት ቃል አቀባይ የሆኑትን ብርጋዲየር ጄኔራል አብዱል ጃሊል አብዱል ራሁምን ጠቅሶ የፈረንሳይ ዜና ወኪል ዘግቧል።

ከመንግሥት ኮሚሽን እና ከዕርዳታ ድርጅቶች የወጡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በጎርፉ እና በከባድ ዝናብ ሳቢያ በተለያዩ የአገሪቱ ግዛቶች ውስጥ መጠናቸው ከ130 ሺህ በላይ ሰዎች ለችግር ተጋልጠዋል። ከእነዚህም መካከል የማዕከላዊ ዳርፉር፣ደቡብ ዳርፉር፣ ናይል ሪቨር እና ዋይት ናይል ከሌሎቹ በላቀ በርካታ ሕዝብ ችግር ገጥሞታል።

ጎርፉ በሰው ላይ ካስከተለው ጉዳት ባሻገር በርካታ የጤና ተቋማት፣ የውሃ እና የንጽህና መሠረተ ልማቶችን ማውደሙ ተገልጿል።

በተጨማሪም በመቶዎች የሚቆጠሩ ከብቶች በጎርፉ ሲወሰዱ፣ ወደ 20 ስኩዌር ኪሎ ሜትር የሚጠጋ የእርሻ መሬት ጉዳት ደርሶበታል።

የሱዳን የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ዕቅድ እንዳመለከተው በየዓመቱ በርካታ ሕዝብ በጎርፍ ሳቢያ ጉዳት እየደረሰበት ቢቆይም በአሁኑ ዓመት የተከሰተው ይህ ጉዳት ካለፉት ዓመታት ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ነው።

በሱዳን ውስጥ የአባይ ወንዝ መጠን ካለፈው ሐምሌ ወር መጨረሻ ላይ አንስቶ እየጨመረ መሆኑ ተነግሯል።



## ግብፅ የመስኖ እና የውሃ ሚኒስትሯን አሰናብታ በአዲስ ተካች

የግብጹ ፕሬዚዳንት አብዱል ፋታህ አል ሲሲ ጥያቄን ተከትሎ የአገሪቷ ፓርላማ በአገሪቱ የካቢኔ ሚኒስትሮች ላይ ዋነኛ ለውጥ በማድረግ አዳዲስ ሹመቶችን አፀደቀ።

በአዲሱ የግብፅ ካቢኔ ውስጥ ዋነኛ የሚባሉት የመስኖ እና የውሃ ሚኒስትርን ጨምሮ 13 ሚኒስትሮች በአዲስ ሲተኩ፣ የገንዘብ እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች በቦታቸው ቀጥለዋል።

የግብፅን የመስኖ እና ውሃ ሚኒስትርነት ቦታን የተረከቡት አዲሱ ተሿሚ ሃኒ ሴዊላም ሲሆኑ፣ አዲሱ ሚኒስትር በዘርፉ ሦስት አስርት ዓመታት የሚጠጋ ዕውቀትና ልምድ ያካበቱ መሆናቸው ተነግሯል።

ግብፅ ከፍተኛ ትኩረት ከምትሰጣቸው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶቿ መከከል አንዱ የሆነውን እና ኢትዮጵያ ልታጠናቅቀው የተቃረበችውን የታላቁ የኢትየጵያ ሕዳሴ ግድብ ጉዳይን ለዓመታት በቅርበት ሲከታተሉ የነበሩት የመስኖ እና የውሃ ሚኒስትሩ ሞሐመድ አብደል አቲ በአዲስ ተተክተዋል።

ግብጽ የአገሪቱ የካቢኔ ሚኒስትሮች ስብስብ ላይ የመስኖ እና ውሃ ሚኒስትርነት ቦታን ጨምሮ 13 የሚኒስትርነት ቦታዎች ላይ አዳዲስ ሚኒስትሮችን በማካተት ለምክር ቤቱ አቅርባ ማጸደቋን ቢቢሲ ዘግቧል።

ለዚህም በመስከረም ወር መጨረሻ ላይ ሥራውን ለመጀመር ለሦስት ወራት ዕረፍት ተዘግቶ የነበረው የግብፅ ፓርላማ አባላትም “ለአስቸኳይ ጉዳይ” በሚል እንዲሰበሰቡ ተጠርተው አዲስ የቀረቡትን ሚኒስትሮች ሹመት አጽድቀውታል።

የግብፁ ፕሬዚዳንት አብዱል ፋታህ አል ሲሲ በሚኒስተሮቻቸው ላይ ለውጥ ያስፈለገበትን ምክንያት በማኅበራዊ ሚዲያ የትስስር መድረኮች ላይ እንደገለጹት “በአገር ውስጥና በውጪ የአገሪቱን ጥቅም በማስጠበቅና ለዜጎች የሚሰጠውን አገልግሎት የበለጠ በማጎልበት የመንግሥትን የአፈጻጸም ብቃት ለማጠናከር ነው” ብለዋል።

ተሿሚዎቹ ሚኒስትሮች ሥራ ለመጀመር በፕሬዚዳንቱ ፊት ቃለ መሐላ ፈጽመዋል።

ባለፈው ሳምንት በሁለተኛ ተርባይን ኃይል ማመንጨት የጀመረውና ሦስተኛው ዙር የውሃ ሙሌቱን ያከናወነው በአፍሪካ ግዙፉ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ የኢትዮጵያ ግድብ ላይ ግብፅ ለዓመታት ተቃውሞዋን ስታሰማ መቆየቷ ይታወቃል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
ዘመን
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# ማክሰኞ ስፖርት

አዲስ ዘመን

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## የአካዳሚው ፍሬዎችና የወጣት አትሌቲክስ ቡድን ስኬት

ብርሃን ፈይሳ

በእድሜ ገደብ የሚካሄዱ ውድድሮች አትሌቶችን ወደ ስኬታማነት የሚያረማምዱ ድልድዮች መሆናቸው ይታመናል። ለኢትዮጵያዊያን የአሮጌው ዓመት መባቻ እና የአዲሱ ዓመት ስጦታ የሆነው ከ20ዓመት በታች አትሌቲክስ ቻምፒዮና በእርግጥም የወጣት አትሌቶችን ብሩህ ነገ የሚያመላክት ነው። በጥቂት ርቀቶች ተሳትፎ በማጠቃለያው ዕለት ብቻ የተሰበሰቡት 4 ሜዳሊያዎች ዓለምን ሲያስደምሙ፤ ከ19ኙ አትሌቶች 18ቱ ሜዳሊያና ዲፕሎማ ለሃገራቸው ማበርከታቸው ደግሞ የቡድኑን ጥንካሬ ያረጋገጠ ሆኗል።

ታሪክ ሰሪው ቡድን ወደሃገሩ ሲመለስም ከዚህ ቀደም ያልታየ አቀባበልና ማበረታቻ ተደርጎለታል። ይህም ወጣቶቹን አትሌቶች ተተኪና ቀጣይ ሃገራቸውን ተረካቢ እንዲሆኑ ምክንያት እንደሚሆን አመላካች ነው። ታሪካዊና በየትኛውም ውድድር ያልታየውን በርካታ የወርቅ ሜዳሊያ ካስመዘገበው ከዚህ ቡድን በርካታው ስኬት የተመዘገበው ደግሞ በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ፍሬዎች መሆኑም ሌላው አስደናቂ ጉዳይ ነው።

አሰልጣኝ አብዮት ተስፋዬ፤ በ800 እና 1ሺ500 ሜትር የወርቅ እና የብር ሜዳሊያዎችን በማጥለቅ የወደፊት ተስፋውን ያንጸባረቀው አትሌት ኤርሚያስ ግርማ አሰልጣኝ ነው። አትሌቱ በኦሪጎኑ የዓለም ቻምፒዮናም በ800 ሜትር ተሳታፊ መሆኑ አይዘነጋም። በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ አሰልጣኝና የተሳትፎና ውድድር ዳሬክተሩ አብዮት፤ እንደ ቡድን ከውድድሩ



አስቀድሞ ጠንካራ ዝግጅት ሲያደርግ መቆየቱ ለውጤት እንዳበቃቸው ይናገራል። እርሱ የሚያሰለጥነው አትሌት ኤርሚያስ አካዳሚውን ከ2010 ዓም ጀምሮ የተቀላቀለ ሲሆን፤ አሁን ላይ ሃገሩን ከማስጠራት ባለፈ በ800 ሜትር በዓለም ፈጣን ከሚባሉ አትሌቶች መካከል አንዱ የሚያደርገውን ሰዓት አስመዝግቧል።

በመሆኑም መሰል ውድድሮች ታዳጊና ወጣት አትሌቶችን ወደተሻለ ብቃት የሚመራቸው በመሆኑ ሊበረታታ እንደሚገባ አሰልጣኙ ይጠቁማል። እርሱ በሚያሰለጥንበት አካዳሚም ቀጣይነት ያለው ተተኪ አትሌቶችን ማፍራት ላይ አተኩሮ እየሰራ ይገኛል። ለዚህም ማሳያ የሚሆነው በዚህ ውድድር ላይ ተሳታፊ ከነበሩት አትሌቶች መካከል በአካዳሚው እንዲሁም በጥሩነሽ ዲባባ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከል ሰልጣኞች 4 ወርቅ እና 2 ብር ሜዳሊያዎች መቆጠራቸውን ነው። ይኸውም በአትሌት አዲሱ ይሁኔ፣ መልኬነህ አዘዘ፣ ሳሙኤል ድጉና፣ ሳሙኤል ፍሬው፣ ድሪባ ግርማ፣ መብሪት መኮንን የተገኙ ናቸው። በመሆኑም አካዳሚው የውድድር ተሳትፎ ላይ ብቻም ሳይሆን ውጤታማነት ላይም እየሰራ እንደሚገኝ አመላካች መሆኑን ያረጋግጣል።

ከአካዳሚው የተገኙት የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት የሆኑ አቴሌቶችም ለዚህ ስኬት ያበቃቸውና በቀጣይም ሃገራቸውንና ህዝባቸውን ለማኩራት ያላቸውን ዕቅድ ለአዲስ ዘመን እንደሚከተለው ገልጸዋል። በ5ሺ ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ ማጥለቅ የቻለው አትሌት አዲሱ ይሁኔ፤ በውድድሩ አሸናፊ ለመሆን አቅዶ ወደ ካሊ ማቅናቱን ያስታውሳል። በኦሪጎን በተካሄደው የዓለም ቻምፒዮና ኢትዮጵያ ያስመዘገበችው ውጤት ለተወዳዳሪዎች የሞራል ስንቅ ሲሆን፤ ተነሳሽነትን አሳድሮባቸዋል። አትሌቶች ከአሰልጣኞች እንዲሁም ከሌሎች የቡድን አባላት ጋር የነበራቸው ግንኙነትም መልካም መሆኑ አስተዋጽኦ ነበረው። እርሱና ጓደኞቹ የወደፊት ተተኪ አትሌት እንደመሆናቸው በቀጣይም ጠንክረው እንደሚሰሩም አትሌቱ ይጠቁማል።

ሌላኛው የ 3ሺ ሜትር ሜዳሊያ ባለቤት መሆን የቻለው አትሌት መልኬነህ አዘዘ፤ ባለፈው ዓመት ኬንያ ላይ በተካሄደው ቻምፒዮና በ1ሺ500 ሜትር የነሃስ ሜዳሊያ ነበር ያስመዘገበው። ክረምቱ አስቸጋሪ ቢያደርገውም ሲያደርጉ የቆዩት ዝግጅት ለውጤት የሚያበቃ እንደሆነ ይገልጻል። በውድድር ወቅትም ከአሰልጣኞች ጋር በመመካከር መሳተፋቸው በርካታና ታሪካዊ ሜዳሊያ እንዲገኝ ምክንያት ሆኗል። በቀጣይም በዓለም ቻምፒዮና እንዲሁም በኦሊምፒክ መድረኮች ተሳትፎ ሜዳሊያ የማስመዝገብ እቅድም አለው።

የ1ሺ500 ሜትር አሸናፊዋና የርቀቱን ክረወሰን የሰበረችው አትሌት ብርቄ ሃየሎም በተመሳሳይ ያደረገችው ዝግጅት ለአሸናፊነት እንዳበቃት ገልጻለች። ከዚህ በኋላ እንደ ኦሊምፒክ ባሉ ትልልቅ ውድድሮች ላይ ተሳትፋ ለሃገሯ የወርቅ ሜዳሊያ የማስመዝገብ ተስፋም ሰንቃለች።

ከዚህ ቻምፒዮና በመነሳት ሃገሯን በተለያዩ ውድድሮች ላይ ካስጠሩት አንጋፋ አትሌቶች መካከል አንዷ መሰለች መልካሙ ናት። አትሌቷ በቡድን መሪነት ወደ ኮሎምቢያ የተጓዘች ሲሆን፤ በካሊ የነበረው የአየር ሁኔታ ከኢትዮጵያ ጋር የሚመሳሰል መሆኑ አትሌቶች ብዙም ሳይቸገሩ አሸናፊ እንዲሆኑ እገዛ እንዳደረገላቸው ገልጻለች። ቡድኑ ወደ ሃገሩ ሲመለስም ከዚህ ቀደም ከነበረው የደመቀ አቀባበል የተደረገለት መሆኑ አበረታች ነው። ወደፊት ተተኪ የሚሆኑ አትሌቶችን በዚህ መልክ መደገፍ አስፈላጊ መሆኑን ጠቁማለች።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
Ethiopian Cooperative Commission
(ECC)
ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር
በየሳምንቱ የሚታተም

## ለኅብረት ሥራ ዩኒየኑ እድገት የ‹‹ጢባ›› አበርክቶ

አባቴነህ በየነ

የቤንች ሸኮ (ቤንች ማጂ) ዞን በቅርቡ በተደረገው ሕዝብ ውሳኔ ከኅዳር 14 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ መልክ ተዋቅሮ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በመባል በሚታወቀውና መቀመጫውን በሚዛን አማን ከተማ ባደረገው ክልል የሚገኝ ነው። በአካባቢው በርካታ ብሔር ብሔረሰቦች የሚኖሩ ሲሆን እንደ ዲዚ፣ ሱሪ፣ ሸኮ፣ ካፋ፣ ሸካ፣ መዠንግር፣ ቤንችና መኢኒት ያሉ ብሔረሰቦች በዞኑ ተወላጅነት በኅብረት እና በመደጋገፍ ይኖራሉ።

በቀጠናው የሚገኙት ሁሉም ዞኖች በተፈጥሮ ሀብት ጸጋ የተቸራቸው ናቸው። የቤንች ማጂ ዞን በዩኔስኮ ተመዝግቦ የሚገኘውን ጥቅጥቅና ጥብቅ የተፈጥሮ ደን በጉያው ሸሽጎ የያዘ መሆኑ በተፈጥሮ መታደሉን የሚመሰክርበት አንዱ ማሳያው ነው። በተጨማሪም ተፈጥሯዊ የጫካ ቡና፣ ባለ ድንቅ ጣዕም ተፈጥሯዊ ማር እንዲሁም እጅግ ተፈላጊ የሆኑ የቅመማ ቅመም አይነት ምርቶች የአካባቢው በረከቶች ሲሆኑ እነዚህ ምርቶች በአገር ውስጥና በውጭ አገራት ገበያ እየቀረቡ የሸማቹን ቀልብ ለመሳብ የበቁ ናቸው።

የቤንች ማጂ የጫካ ቡና አምራች ገበሬዎች ኅብረት ሥራ ዩኒየን በአሁኑ ሰዓት የአምራች(ምርት አቅራቢ) አባላቱን ኑሮ በማሻሻል ላይ ይገኛል። ዩኒየኑ የተመሰረተው በ1997 ዓ.ም ሲሆን በወቅቱ የመሰረቱት 14 አባል መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ባቀፏቸው ሁለት ሺ 988 ግለሰብ አባላት የጋራ ስምምነት በመፈጸም ነው። መነሻ ካፒታላቸውም 201 ሺ ብር ብቻ ነበር።

የኅብረት ሥራ ማህበራት በዘርፉ በሰለጠነ(በተማረ) የሰው ኃይል ሲመሩ ውጤታማ መሆናቸው እሙን የመሆኑን ያህል ዩኒየኑን በዕውቀትና በአመራር ስልት መልሶ ማጠናከር በመቻሉ ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ አስደማሚ ውጤት በማስመዝገብ በአፍላ ዕድሜው የብዙሃንን ቀልብ መሳብ ያስቻሉ ለውጦችን አስመዝግቧል።

በፈጣን የዕድገት ግስጋሴ ውስጥ የሚገኘው ይህ ዩኒየን ለዕድገቱ ፍጥነት በምክንያትነት ከሚቀርቡት ጉዳዮች በዋናነት በኅብረት ሥራ መርህዎች ብቻ መመራቱ ሲሆን የተቋሙ አመራር በግልጸኝነት በዕውቀትና በታማኝነት የመምራት ጥበብ እንዲሁም የቦርድ፣ የሥራ አመራር አካላትና ቅጥር ሠራተኞች ከመላው አባላት ጋር ያላቸው ግልጽነት የሰፈነበት መስተጋብር ለመሆኑ ብዙዎች የሚስማሙበት ነው። ከዚህ ባሻገር ግን የማህበሩ ነባር እሴት የሆነው የ‹‹ጢባ›› የዝምድናና የመተማመን ማህበረሰባዊ ፍልስፍና በዩኒየኑ እድገት ላይ የተጫወተው ሚና ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም።

‹‹ጢባ›› ማለት በቤንች ሸኮ ማህበረሰብ ዘንድ እምነት ቋንቋ፣ ቀለምና ሐይማኖት ሳይለይ የዝምድናና ጽኑ የመተማመን አስተሳሰብ ነው። በገጠር የሚኖረው አርሶ አደር ጥሮ ግሮ ያመረተውን የግብርና ምርት(አትክልትና ፍራፍሬ፣ አዝዕርት፣ የቁም እንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ፣ ቡናና ማር እንዲሁም ቅመማቅመም) ለሽያጭ ወደ ገበያ አውጥቶ በአጋጣሚ ገበያው ተስማሚ ዋጋ ባይሰጠው እንኳን ምርቱን መልሶ ወደ ቤቱ አይወስደውም። ይልቁንም እንደ አካባቢው ማኅበረሰብ ወግና ባህል መሰረት በስጋና በደም ለማይዛመደው የከተማ ሰው በአደራ በመስጠት ንብረቱን ሸጦ ዋጋውን(ገንዘቡን) በሌላ ጊዜ እንዲሰጠው ያደርጋል። አደራ የተቀበለውም የከተማ ሰው ቃሉን ሳያጓድል የተረከበውን ንብረት ሸጦ ለባለቤቱ ያስረክበዋል። ‹‹ጢባ›› የመተማመን ዋስትና ሚሰጥ ባህላዊ እሴት በመሆኑ በግብይት ሥርዓት ውስጥ ሸማችና ሻጭ በመተማመን ላይ የተመሰረተ ግንኙነት እንዲኖራቸው ስለሚያስችል ለኅብረት ሥራ መርህዎች መደላድል ሆኗል።

ከኅብረት ሥራ ማህበራት እሴቶች ዋነኛው ወንድማማችነት ሲሆን ከአባላት የስነ-ምግባር እሴቶችም የላቀው ታማኝነት እንደሆነ የተለያዩ በዘርፉ የተከተቡ

**ከኅብረት ሥራ ማህበራት እሴቶች ዋነኛው ወንድማማችነት ሲሆን ከአባላት የስነ-ምግባር እሴቶችም የላቀው ታማኝነት እንደሆነ የተለያዩ በዘርፉ የተከተቡ ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡ ‹‹ጢባ›› በዝምድና መርህ ላይ የተመሰረተ የሁለትዮሽ ወይም የእርስ በርስ መተማመን ነው**

ድርሳናት ያስረዳሉ። ‹‹ጢባ›› በዝምድና መርህ ላይ የተመሰረተ የሁለትዮሽ ወይም የእርስ በርስ መተማመን ነው። ለቤንች ማጂ የጫካ ቡና አምራች ገበሬዎች ኅብረት ሥራ ዩኒየን ፈጣን ዕድገት በምክንያትነት ሊጠቀስ የቻለውም አባላት ምርቶቻቸውን በፈቃዳቸው ለመሰረቷቸው መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት በማስረከብ በተሻለ ዋጋ ተሸጦ እንዲሰጧቸው ስለሚያደርጉ ነው። መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራቱ በጣምራ ለመሰረቱት ዩኒየናቸው ምርቶቻቸውን በማስረከብና በዓለም አቀፍ ገበያ በተሻለ ዋጋ ተሽጦ እንዲስጣቸው በማድረግ የጋራ ተሳትፎና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እንዲሰፍን በማድረግ ኢኮኖሚያዊ እድገታቸውን እንዲያረጋግጡ ረድቷቸዋል።

የኅብረት ሥራን ዓለም አቀፍ መርህ ከ‹‹ጢባ›› የቤንች ማህበረሰብ የዝምድናና የመተማመን ፍልስፍና ጋር በማዋሃድ የዩኒየኑ የአስር(10) ዓመታት የግብርና ልማትና ግብይት ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ ተችሏል። ለአብነት ያህል የግለሰብ አባላቱን ቁጥር ከ2ሺ 988 ወደ 20ሺ በላይ ማሳደግ ተችሏል። 14 ብቻ የነበሩትን አባል መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት 85 በማድረስ፤ካፒታሉንም ከ75 ሚሊዮን ብር በላይ በማሳደግ በአባላት የኑሮ መሻሻል ላይ ጉልህ ሚና እየተጫወተ ይገኛል።

ዩኒየኑ በሚከተላቸው አሠራሮች ለምሳሌ በ1ለ10 የስልጠናና የመረጃ ስርጭት ልማታዊ አደረጃጀትና አተገባበር አምራቾችን ተመሳሳይ ዕውቀት በማስጨበጥ ባስመዘገበው ውጤት ከአባላቱ ተጠቃሚነት ባሻገር ለአካባቢው ተስፋ ሆኗል። በተከታታይ ለውጭ ገበያ በሚያቀርባቸው የቡና፣የማርና ቅመማ ቅመም ምርቶች ግብይት በዓለም አቀፍ ገዢዎች ተመራጭነቱ እያደገ መጥቷል። በማህበራዊ አገልግሎት ተግባራት በተለያዩ የዞኑ ወረዳዎች የኅብረተሰቡን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በመቅረፍ ታላላቅ ተግባራትን በመፈጸም ላይ ይገኛል። በርካታ የቡናና የማር ምረት ማምረቻና ጥራት ማስጠበቂያ ኢንዱስትሪዎችን በማነጽ ለበርካቶች የሥራ ዕድል ዋስትና ከመሆኑም በላይ በዞኑ የልማት ፎረሞችን በበላይነት በማዘጋጀት በንግድና ቱሪዝም ዘርፍ እንዲሁም በአካባቢው በሚደረጉ የልማት እንቅስቃሴዎች ላይ ፋና ወጊ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል።

የ‹‹ጢባን›› የዝምድናና የእርስ በርስ መተማመን መርህ በማዳበር የቤንች ማጂ የጫካ ቡና አምራች ገበሬዎች ኅብረት ሥራ ዩኒየን የምርትና የገበያ ድርሻውን አሳድጎ ዘላቂና ተከታታይ ዕድገት በማስመዝገብ በአባላት አኗኗር ላይ ተጨባጭ መሻሻልን እንደሚያጎለብት የዩኒየኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ጌታሁን ተክሌ አረጋግጠዋል። ለዚህም እቅድ መሳካት ከጥቅምት 4-5 2015 ዓ.ም 13ኛውን ጠቅላላ መደበኛ ጉባዔ ለማድረግ ዝግጅት ላይ ያሉ ሲሆን ያለፈውን የሥራ ክንውን በመገምገም የቀጣዩን ዓመት የሥራ እቅድ በጉባዔው በማስጸደቅ ወደ ትግበራ ገብተው ከቀደመው የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ መዘጋጀታቸውን ተናግረዋል።

አድራሻ | የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Federal cooperative Agency | Website: www.fca.gov.et

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ